መቐለ ዩኒቨርሲቲ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የክረምት ድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር በማስተማር ስነ-ዘዴ ኤምኤ ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

# በ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ (በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን በስለዋ ወረዳ ወዲ ሽረ ት/ቤት)

በ

ኣብሪሃ ኣሰፋው ኣድሀና

ታህሳስ- 2018 ዓ.ም

መቐለ- ኢትዮጵያ

# በ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ (በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን በስለዋ ወረዳ ወዲ ሽረ ት/ቤት)

በ

ኣብረሃ ኣሰፋው ኣድሀና

መቐለ ዩኒቨርሲቲ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የክረምት ድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር በማስተማር ስነ-ዘዴ ኤምኤ ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

ለ

ዋና አማካሪ፦ ተኽለሃማኖት ገ/ፃድቅ(ዶር)

ረዳት አማካሪ፦ ተስፋይ ሞላ

ታህሳስ- 2018 ዓ.ም

መቐለ- ኢትዮጵያ

## መቐለ ዩኒቨርሲቲ

## የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የክረምት ድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር በማስተማር ስነ-ዘዴ ኤምኤ ድግሪ ከፊል ማሟያ የቀረበ ጥናት

# በ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሓፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ (በትግራይ ክልል ደቡባዊ ዞን በስለዋ ወረዳ ወዲ ሽረ ት/ቤት)

በ

ኣብሪሃ ኣሰፋው ኣድሀና

ታህሳስ- 2018 ዓ.ም

## የፈተና ቦርድ አባላት

| ስም | ፊርማ |
|---|---|
| 1.ዋና አማካሪ፡- ተኽለሃማኖት ገ/ፃድቅ(ዶር) | -------- |
| 2.ረዳት አማካሪ፡- ተስፋይ ሞላ | --------- |
| 3.ፈታኝ ፡- ---------------------------- | ---------- |

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለዚህ ደረጃ ያደረሰኝ ልዑል እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው፡፡በመቀጠል ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ እዚህ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ሳይሰለቹ ክፍተቶቼን በማሳየት፣ ሙያዊ ድጋፋቸውን ለሰጡኝ ለዋና አማካሪዬ ለዶር ተኽለሃይማኖት ገብረፃዲቅ እንዲሁም ለረዳት አማካሪዬ ተስፋይ ሞላ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል የድህረ ምረቃ ትምህርቴን ከመጀመሪያ እስካሁን ድረስ ያስተማሩኝን አስተማሪዎቼን በሙሉ አመሰግናለሁ፡፡ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ ለመቐለ ዩኒቨርሲቲ ቤተ-መፅሀፍት ሠራተኞች በሙሉ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ጥናቱ እንዲሳካ ውድ ጊዜያቸውን ሳይሰስቱ ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ለሰጡኝ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሙሉ ባሉበት ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ትምህርቴን ጀምሬ እስከምጨርስ ከጎኔ በመሆን ለአበረታታቹሁኝ ቤተሰቦቼ በተለይም የጥናቱን ጽሁፍ በኮምፒውተር ለፃፈልኝ ውድ ባለቤቴ እጅግ አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ለወ/ት ሃይማኖት በሪሁን ላደረገችልኝ ሙያዊ ድጋፍ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

**ምስጋና**.......................................................................................................I

**ማውጫ**.......................................................................................................IV

**የሠንጠረዥ ማውጫ** ....................................................................................... VII

**አህፅሮተ ጥናት**.......................................................................................................VIII

**ሙዳዬ ቃላት**.......................................................................................................IX

**ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ** ....................................................................................... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ .......................................................................................................1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች .......................................................................................................3

1.3 የጥናቱ ዓላማ .......................................................................................................4

1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ.......................................................................................................4

1.3.2 ዝርዝር ዓላማዎች .......................................................................................................4

1.4 የጥናቱ ጥያቄዎች ---------------------------------------------------------------------------4

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ .......................................................................................................4

1.6 የጥናቱ ወሰን.......................................................................................................5

1.7 የጥናቱ ውስንነት.......................................................................................................5

**ምዕራፍ ሁለት፡ የተዘማጅ ድርሳናት ክለሳ** ....................................................................................... 6

2.1 የንድፈ-ሀሳብ ክለሳ .......................................................................................................6

2.1.1 ቃል.......................................................................................................6

2.1.2 የቃላት ትምህርት ምንነት .......................................................................................................7

2.1.3 የቃለት ትምህርት አስፈላጊነት .......................................................................................................9

2.1.4 የቃላት ትምህርት ይዘቶች ማቅረቢያ ስልቶች.......................................................................................................11

2.1.4.1 ቃላትን በአውድ ማቅረብ .......................................................................................................12

2.1.4.2 ቃላትን በፍች ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ.......................................................................................................13

2.1.4.2.1 ቃላትን በተመሳስሎና በተቃርኖ ፍችያቸው ማቅረብ.......................................................................................................14

2.1.4.2.2 የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት .......................................................................................................14

2.1.4.2.3 የቃላት አብሮ ተሰላፊነት .......................................................................................................15

2.1.4.2.4 ቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ.................................15
2.1.4.2.4 ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ .................................................16
2.1.5 የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ...........................................................18
2.1.5.1. የተማሪውን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ.....................................................18
2.1.5.2. የቃላት የፍች ሽፋን...........................................................................19
2.1.5.3. የቃላት የድግግሞሽ መጠን ....................................................................20
2.1.5.4. ባህላዊ ተላውጦ..................................................................................21
2.1.5.5. የቃሉ ተስተማሪነት.............................................................................22
2.1.6. የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀት...........................................................22
2.1.6.1 ከቀላል ወደ ከባድ ማደራጀት ..................................................................23
2.1.6.3 ቃላትን በፍች ማደራጀት .......................................................................24
2.1.6.4 ቃላትን በቅርፅ ማደራጀት......................................................................25
2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ..........................................................................26
**ምዕራፍ ሶስት፡ የጥናቱ ዘዴ እና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች............................................ 28**
3.1 የጥናት አይነት .....................................................................................28
3.2 የመረጃ ምንጭና የናሙና አወሳሰድ ...............................................................28
3.2.1 የዞንና የወረዳ ናሙና አመራረጥ ..............................................................28
3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ............................................................28
3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ...................................................................29
3.2.4 የመማሪያ መጽሀፍ ናሙና አመራረጥ..........................................................29
3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ .....................................................................29
3.3.1. ሰነድ ፍተሻ.......................................................................................29
3.2.2. ቃለመጠየቅ ......................................................................................30
3.4 የመረጃ ትንተና.....................................................................................31
3.4.1 ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ አተናተን..........................................................31
3.5.2 የቃለመጠይቅ አተናተን ..........................................................................31
**ምዕራፍ አራት፡ የመረጃ ትንተና ........................................................................... 32**
4.1. የተተኳሪው መማሪያ መፅሀፍ ዳራ .............................................................32

4.2 በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መረጃ ................................33
4.2.1 ከሰነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ..........................................34
4.2.1. 1. የቃላት ትምህርቱን አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና ...................................34
4.2.1.1.1. የቃላት ትምህርቱን አውዲዊ አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና .....................35
4.2.1.1.2. የቃላትን የፍች ዝምድና አቀራረብ የተመለከተ መረጃዎች ትንተና ............................37
4.2.1.1.3. ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ .............................................................40
4.2.1.1.4 ቃላትን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ ...............................................................41
4.2.1.1.5 ቃላትን ከክሂል ትምህርቶች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ ..................................................43
4.2.1.1.6 የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና ...........................44
4.2.1.2 የቃላት ትምህርትን ይዘት አመራረጥ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና ...........................46
4.2.1.2.1. የተማሪውን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ ..................................................................46
4.2.1.2.2. የቃላት የድግግሞሽ መጠን ..................................................................................47
4.2.1.2.3.የቃላት የፍች ሽፋን ............................................................................................49
4.2.1.2.4. የቃሉ ተስተማሪነት.............................................................................................50
4.2.1.2.5. ባህላዊ ተላውጦ ..................................................................................................51
4.2.1.3. ከቃላት ትምህርት አደረጃጀት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና......................................52
4.2.1.3.1. ቃላትን ከቀላል ወደ ከባድ ከማደራጀት አንጻር .........................................................53
4.2.1.3.2. ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርጎ ከማደራጀት አንጻር ....................................................54
4.2.1.3.3. ፍችን መሠረት አድርጎ ከማደራጀት አንጻር...............................................................54
4.2.1.3.4. ቅርፅን መሠረት አድርጎ ከማደራጀት አንጻር .............................................................56
**ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያና አስተያየት ....................................................................... 59**
5.1 ማጠቃለያ ..........................................................................................................59
5.2. አስተያየት...........................................................................................................60
**ዋቢዎች ...................................................................................................................... 62**
**አባሪዎች ..................................................................................................................... 66**

## የሠንጠረዥ ማውጫ

| የሠንጠረዥ ቁጥር | የሠንጠረዥ ርዕስ | ገፅ |
| --- | --- | --- |


ሰንጠረዥ1. የተተኳሪ መጽሀፍ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ........ 33
ሰንጠረዥ 2. በመማሪያ መጽሀፉ የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ ........ 35
ሠንጠረዥ 3. የቃላት ትምህርት የፍች ዝምድና አቀራረብ ........ 37
ሠንጠረዥ4. መዝገበ ቃላትን ተደግፈው የቀረቡት ቃላት ........ 40
ሠንጠረዥ 5. የቃላት ትምህርት ተግባራት የመመሪያዎች አቀራረብ ........ 42
ሠንጠረዥ 6. የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አቀራረብ ........ 43
ሠንጠረዥ 7. የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት በተመለከተ ያላቸው አቀራረብ ........ 45
ሠንጠረዥ 8. የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት በተመለከተ ያላቸው አቀራረብ ........ 46
ሠንጠረዥ 9. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ይዘት የድግግሞሽ መጠን ........ 48
ሠንጠረዥ 10. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱ ምንባቦች ........ 51
ሠንጠረዥ11. የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መልመጃዎች ........ 55
ሠንጠረዥ12. የእርባታ ወይም የምስረታ ቅጥያዎች ........ 57

// አህፅሮተ ጥናት

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው እና በ2015 ዓ.ም በስራ ላይ የዋለው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ ነው። ይህንንም አላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የተከተለው አይነታዊ የምርምር ዘዴን ነው፡፡ ጥናቱን የተለያዩ ምሁራን ስለ ቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብ ባነሷቸው ንድፍ ሀሳባዊ መስፈርቶችና መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ በመማሪያ መጽሀፉ ላይ የሠነድ ፍተሻ እና ለመምህራን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ አስፈላጊው መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በመቀጠልም ከሰነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በአይነት በአይነት በመመደብ የመተንተን ስራው ተከናውኗል፡፡ የትንተናው ውጤትም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በተመለከተ በበቂ ሁኔታ ያልተደራጁ መሆናቸው፣ በፍች ዝምድና ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ውስንነት ያለበት መሆኑ፣ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አኳያ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው ክፍተት መሆኑ፣መጽሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራትን በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የማቅረብ ክፍተት ያለበት መሆኑ በድክመት ተነስቷል፡፡

## ሙዳዬ ቃላት

| ቃል/ሐረግ በመገኛ ቋንቋው | የአማርኛ ፍችው |
|---|---|
| Abstractness | ረቂቅነት |
| Pronunciation | የቃላትን ትክክለኛ አጠራር |
| Spelling | አጻጻፍ |
| Availability | በቅርብ መገኘት |
| Collocations | አብሮ ተሰላፊ |
| Binary Antonyms | ተጻራሪ/ የጥንድ ተቃርኖ |
| Concretness | የቃላት ተጨባጭነት |
| Compounding | ጥመራ |
| Denotation | እማሬ |
| Derivation | ምስረታ |
| Connotation | ፍካሬ |
| Conversances | የተገላብጦሽ ተቃርኖ |
| Cultural factor | ባህላዊ ተላውጦ |
| Gradable Antonyms | ተደራጅ ተቃርኖ |
| Hyponym | ተከታች |
| Infletion | እርባታ |
| Learnability | ተስተማሪነት |
| Super Ordinate | ከታች |
| Dictionary | መዝገበ ቃላት |
| Directionality Antonyms | ባለአቅጣጫ ተቃርኖ |

# ምዕራፍ አንድ፡ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ የሰው ልጅ መግባቢያና የሐሳብ መለዋወጫ መሠረታዊ መሣሪያ ነው፡፡ ቋንቋ የባህልና ማንነት መገለጫ ከመሆኑም በላይ ትውልዶች እሴቶቻቸውን እንዲጠብቁ ያግዛል (አበባው፣ 2021: 85)፡፡ ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግሉ መማሪያ መጻሕፍት፣ ስነትምህርትና በቋንቋ ሳይንስ መርሆች ላይ ተመስርተው በተገቢው መንገድ ከተዘጋጁ፣ የመማር ማስተማሩ ሂደት ለተማሪውም ሆነ ለመምህሩ ቀላል እንዲሆንና ፍሬያማ ውጤት እንዲያስገኝ በማድረግ በኩል ያላቸው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ Hutchinson and Torres (1994, 315) እንደሚገልጹት ተማሪዎች በትምህርት ሂደቱ ውይይት ሲያካሂዱ፣ መልመጃዎችን ሲሠሩ፣ የቋንቋ ተግባራትን ሲያከናውኑ፣ ሲያጠኑ፣ የቤት ሥራ ሲሠሩ፣ ለፈተና ሲዘጋጁ ወዘተ መማሪያ መጽሐፍትን ይጠቀማሉ፡፡

እንደ Dubin and Olishtain (1986) አገላለፅ፣ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስበው የሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት የታላሚውን ቋንቋ ክሂሎች ለማዳበር የሚረዱ ይዘቶችን አቀናብረው የያዙና የቋንቋውን ስነልሳናዊና ስነትምህርታዊ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ስነልሳናዊ ይዘቶች ስንል በታላሚው ቋንቋ ውስጥ ያሉትን ድምፆች፣ ቃላት፣ ዓረፍተነገሮች፣ ወዘተ ይመለከታል፡፡ ይህም አንድ ድምፅ ከሌላ ድምፅ ጋር ሲቀናጅ ምን አይነት ባህሪ እንደሚያሳይ፣ አንድ ቃል በዓረፍተነገር ውስጥ ያለውን አገባብና አገልግሎት ምን እንደሚመስልና ምን ላይ ማተኮር እንዳለብን ለመወሰን ይረዳል፡፡ ስነትምህርታዊ ይዘት ስንል ደግሞ ተማሪው ቀድሞ ምን ተምሯል?፣ አሁን ምን አይነት ይዘት ይፈልጋል?፣በቋንቋ ምን መጠቀም ይፈልጋል?፣ ይዘቶች እንዴት መቅረብ አለባቸው? እና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ይመለከታል፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የትምህርቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በስፋት ከሚያካትቷቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ዉስጥ ቃላት ተጠቃሽ እንደሆኑ ከላይ ለመግለፅ ተሞክሯል፡፡ seal (1991) እንደገለፁት የአንድ ቋንቋ ቃላት በህንፃ ጡብ ይመሰላሉ፣ በእነሱም ላይ በመመስረት የቋንቋ እውቀት ይገነባል፡፡ መሰረታዊ የቋንቋ አካላት በመሆናቸውም አንድ ሰው በቂ የቃላት እውቀት ከሌለው ሃሳቡን በተሳካ ሁኔታ ሊገልፅም ሆነ የሌሎችን ሃሳብ ሊቀበል አይችልም፡፡ እንዲሁም McCarthy (1990) እንደሚገልፁት የማንኛውም ቋንቋ ትምህርት ወሳኝ አካላት ቃላት ናቸው፡፡ ቃላት ፍችን የመሸከም ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡ በተለይም ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩበት ጊዜ

የቃላት ክምችት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ እንደ Richards & Rodgers (2014) ገለጻ፣ የቃላት ፍችን የመሸከም ከፍተኛ አስተዋፅኦ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የቃለት ጥናት ዋነኛ ተተኳሪ ጉዳይ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

የቃላት ትምህርት ምንነት ስንመለከት፣ ተማሪዎች በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉትን ቃላት በተለያዩ መንገዶች ሊማሩ ይችላሉ፡፡ የመጀመሪያው መንገድ በቋንቋው ለማዳ ሂደት ውስጥ ከሚያገኟቸው ሰዎችና ከአካባቢያቸው በመደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚማሩበት ነው፡፡ ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በመደበኛ መንገድ በትምህርት ቤት የሚማሩበት ነው፡፡ በመደበኛ መንገድ የሚካሄደው የቃላት ትምህርት፣ አንድ ተማሪ በክፍል ውስጥ ከሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት አዳዲስ ቃላትን የሚተዋወቅበት ሂደት ነው፡፡ የቃላት ትምህርት ለሌሎች የክህሎት ትምህርቶችም ሆነ ለሰዋስው ትምህርት መሰረት ነው፡፡ ተማሪዎች ቃላትን በአግባቡ ካልተማሩ፣ ቃላት የት ቦታ ከማን ጋር እንደሚጣመሩ ሳይረዱ ይችላሉ፡፡

Dubin and Olishtain (1986፣42) እንደሚገልጹት ቃላትን ለማስተማር የምንጓዝባቸው ሁሉም ስልቶች ወይም ሂደቶች እኩል ውጤታማ አይሆኑም፡፡ቃላትን ለማስተማር በቅድሚያ የማስተማሪያ ዘዴውን ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች በቀላሉ የቃላት እውቀታቸውን ሊያዳብሩና ሊያሻሽሉ የሚችሉት በየትኛው የማስተማሪያ ስልት ቢማሩ ነው? አይረሴ የሚሆነውንና ለተማሪዎች አዝናኝ እና ትኩረትን የሚስበውን የማስተማሪያ ዘዴ መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ መምህራን ቃላትን ለማስተማር የሚጠቀሙባቸው ስልቶች (ዘዴዎች) በርካታ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ቃላትን አንድ ወጥ በሆነ የማስተማሪያ መንገድ ወይም ስልት ማስተማር አይቻልምና፡፡ ምክንያቱም ከቃሉ ባህሪያት፣ ከሚኖራቸው የፍች ልዩነት፣ ከአገባባቸው ወዘተ. ጋር በተያያዘ፡፡

የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የተቀናበረ የቃላት ትምህረት እንዲይዙ በተለያየ ጊዜ ግምገማ በማካሄድ ድክመታቸውን ለማሻሻል ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ እንደ Elley (1989) ገለፃ፣ ግምገማ የቋንቋ ትምህረት መርሀግብር አካል ነው፡፡ በመሆኑም ተከታታይ ግምገማዎችን በማካሄድ የግምገማ ውጤቱን ተመርኩዞ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት የቋንቋ ትምህርት ደካማ ጎኖችን ለማስተካከልና የትምህርቱን ጥራት ለመጠበቅ ያስችላል፡፡ ስለዚህ በየጊዜው የሚታተሙ የቋንቋ የመማሪያ መፃህፍት የሚፈለገውን ዓላማ ከግብ እንዲያደርሱ ከተፈለገ የይዘት አመራረጣቸውንና አቀራረባቸውን መገምገም ያስፈልጋል፡፡

አሁን ባለው የሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ የአንደኛ ደረጃ መማሪያ መፃህፍት የሚዘጋጁት በክልሎች ነው፡፡ በክልሎች ከሚዘጋጁ መማሪያ መፃህፍት መካካል በ2015 ዓ.ም በትግራይ ክልል ስራ ላይ የዋለው የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የአማሪኛ መማሪያ መፅሀፍ ተጠቃሽ ነው፡፡ የዚህ ጥናት አብይ ትኩረትም በስራ ላይ ያለውን ትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት በማድረግ በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል እንዲያገለግል በተግባር ላይ የዋለውን የአማሪኛ መማሪያ መፅሀፍ የቃላት ትምህርትን በማስተማር ረገድ ምን እንደሚመስል መገምገም ይሆናል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

አጥኚዋ በትግራይ ክልል በ2015 ዓ.ም ሥራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ጥናት እንድታካሂድ ያነሳሷት ምክንያቶች እነዚህ ናቸው፡-

1ኛ. አጥኚዋ ካለፉት አመታት የማስተማር ልምዷና ከአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር ካደረገቻቸው ኢ-መደበኛ ውይይቶች የአማሪኛ መፃሕፍት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ የትምህርት እርከኑን የሚመጠኑ ቃላት መረጣ በተወሰኑ መስፈርቶች የተከሄዱ ቢሆኑም ሁሉንም አለመካተቱና በመጽሀፉ  የቃላት ትምህርት ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ፤ በምሳሌና በተብራራ መልኩ ያልቀረቡ ግልፅነት የሚጎድላቸው የተወሰኑ መልመጃዎች መኖራቸው ተጠቃሽ ናቸው፡፡፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ ለቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አዎንታዊ አመለካከት እያሳጣ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ይህ ችግር አዲሱ መጽሐፍ ፈትቶት እንደሆነ ለማወቅና መጽሐፉ ቃላትን የመረዳት ችሎታቸው ላይ በጎ ተጽዕኖ እንዳለው ይገመገማል፡፡

2ኛ. የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች ሲፈተሹ ችግሮች እንደነበሩ ተረጋግጧል፡፡ ለምሳሌ፣ ቀደምት ጥናቶች እንደሚያሳዩት መጻሕፍት ለቃላት ትምህርት በቂ ትኩረት አይሰጡም፣አልፎ ተርፎም መልመጃዎቹ ግልጽ አይደሉም፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች መካከል አልማዝ (2012) እና ሞላ (2003) ጥናቶቻቸው የቃላት ትምህርት አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ ያደረጉ ናቸው፡፡

ከላይ ባነሳቻቸው በተለያየ ጊዜና ቦታ በቃላት ትምህርት ይዘት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ውስጥ የታዩ ጉድለቶች በዚህ ጥናት ተተኳሪ በተደረገው መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መኖር ያለመኖራቸው ወይም መታየት ያለ መታየታቸው ለመገምገም ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

### 1.3.1 አጠቃላይ ዓላማ

የጥናቱ አጠቃላይ ዓላማ በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ መገምገም ነው።

### 1.3.2 ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ ከዋናው ዓላማ የመነጩ የሚከተሉት ንዑስ ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

- የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፃሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለመምረጥ በስራ ላይ የዋሉት የቃላት ይዘት መምረጫ መስፈርቶች መገምገም፤
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘረዘሩት የቃላት ትምህርቶች ማቅረቢያ ስልቶችን በመጠቀም መቅረብ አለመቅረባቸውን መፈተሽ፤
- በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ መገምገም የሚሉት ናቸው።

## 1.4 የጥናቱ ጥያቄዎች

የዚህ ጥናት መሰረታዊ ጥያቄዎች የሚከተለት ናቸው፡-

- የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፃሃፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ለመምረጥ ተባራዊ የተደረጉ የቃላት ይዘት መምረጫ መስፈርቶች አካታች ናቸው ወይ?
- በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተዘረዘሩትን የቃላት ትምህርቶች ማቅረቢያ ስሌቶችን በመጠቀም ቀርበዋል ወይ?
- በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ምን ይመስላሉ? የሚሉት ናቸው።

## 1.4 የጥናቱ ጠቀሜታ

8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ ጥናትና ምርምር ሊኖረው የሚችለውን ጠቀሜታ ከዚህ በታች በተለያዩ ደረጃዎች ተዘርዝሯል።

**ሀ. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን፡-**መምህራን የቃላት ትምህርትን እንዴት በተሻለ መንገድ ማስተማር እንደሚችሉ እንዲረዱና በተማሪዎቻቸው ዘንድ የቃላት ክምችት እንዲጨምር እና የቋንቋ ችሎታቸው እንዲሻሻል የሚረዱ ዘዴዎችን እንዲጠቀሙ ያነሳሳቸዋል፡፡

**ለ. ለመማሪያ መጽሀፍ እና ለመርሀ ትምህርት አዘጋጆች፡-** በመጽሀፍ ዝግጅት ወቅት በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የሚካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ምን መምሰል እንደሚገባቸው ፍንጭ ይሰጣል፡፡

**ሐ. ለጥናት አድራጊዎች፡-** በቃላት ትምህርት ይዘቶች  አቀራረብ ዙሪያ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች የመነሻ ሀሳብ እንዲሁም ማጣቀሻ በመሆን ያገለግላል ተብሎ ይታሰባል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናት ወሰን በ2015 ዓ.ም በትግራይ ክልል ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ በማተኮር አጥኚዋ በመረጠችው በስለዋ ወረዳ ወዲ ሽረ ት/ቤት ከሰነድ ትንተና በተጨማሪ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቃለ መጠይቅ እንደ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ተጠቅማለች፡፡ ከቋንቋ ይዘቶች አንጻር ይህ ጥናት ትኩረቱን በቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ላይ ብቻ ተደርገዋል፡፡ በመሆኑም በመፅሀፉ የቀረቡ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችና በስነ ፅሁፍ ላይ ያተኮሩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች አመራረጥና አቀራረብ አይመለከተም፡፡ በሌላም በኩል በቃላት ትምህርት አሰጣጥ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና የመምህራን የቃላት ትምህርት አተገባበር ከዚህ ጥናት ወሰን ውጭ ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የጥናቱ ዓለማ በተቀመጠለት ግዜ ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ለመጠናቀቅ ታስቦ ነው፡፡

## 1.6 የጥናቱ ውስንነት

የመሰብሰብና የመተንተን ስራው በሚከናወንበት ጊዜ የሰዓት ማጠር ወይም የጊዜ መጣበብና የኢንተርኔት አገልግሎት መቆራረጥ ይኖራል፡፡በተጨማሪም ጥናቱ የሚካሄደው ከስራ ጎን ለጎን በመሆኑም ከመደበኛው ክፍለ ግዜ ውጭ ሰዓት በማመቻቸት መረጃዎችን በቅርብ ያለማግኘት እንደተግዳሮች የሚጠቀሱ ናቸው፡፡አጥኚዋ እነዚህ ተግዳሮቶች በመፍታት ረገድ ያስቀመጠችው መፍትሄ በወጣው ጊዜ ሰሌዳ መሰረት ስራዎች ማከናወንና የኢንተርነት ጥቅል አገልግሎት በመግዛት ከኢንተርኔት መረጃ በመሰብሰብ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት፡ የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ የጥናቱን ድርሳናት ክለሳ ማቅረብ ሲሆን ለጥናቱ ወሳኝ የሆኑ መሠረታዊ ነጥቦችን ከተለያዩ መጻሕፍት፣ ከታተሙና ካልታተሙ ጥናታዊ ሥራዎች እና ሌሎች የመረጃ ምንጮች ዋቢ በማድረግ ይብራራበታል። እነዚህ መሠረታዊ ነጥቦች በሚከተሉት ዋና ዋና ርዕሶች ይከፈላሉ፦ የቃላት ትምህርት ምንነትና የቃላት ትምህርት አቀራረብ ላይ ሀሳባዊ ቅኝት ከጥናቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ ቀደምት ጥናቶች ክለሳ እንደሚከተለው በቅደም ተከተል ቀርበዋል።

## 2.1 የንድፈ-ሀሳብ ክለሳ

### 2.1.1 ቃል

ቃል ማለት የሰው ልጅ አብሮ ከመኖር የተነሳ ወይም የተደራረበ የንግግር ድምፅን አንድ አይነት ፍች ወይም ትርጉም በማስያዝ ሀሳቡን፣ ስሜቱን፣ ፍላጎቱን ወይም በአካባቢው የሚገኘውን ነገር የሚገልፅበት የመግባቢያና የመገናኛ አይነተኛ መሳሪያ ነው።በቅርብ የህብረተሰብ ግንኙነት በማድረግ የሚኖሩ የተወሰኑ ሰዎች እየተግባቡ የሚጠቀሙባቸው ቃላት በአሰካክ ስርዓታቸው አንድ ቋንቋ ይፈጥራሉ የዩኒቨርሲቲ መምህራን የውይይት ማህበር (1980፣7)።

ቃላት መግባቢያ ናቸው። የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች በቃላት ይለማመዳሉ፣ ይግባባሉ፣ እና ይተዋወቃሉ። በሌላ አባባል፣ አንድ ቃል ቢያንስ በዕለት ተዕለት አገልግሎት ውስጥ ተናጋሪዎቹን የሚያግባባ አንድ የተወሰነ ትርጉም አለው (ብርሃኑ፣1999፣73)።

ሰውን ከእንስሳት የሚለየው አንድ መሠረታዊ ባህሪው የንግግር ችሎታው ወይም የቋንቋ ባለቤትነቱ ነው። ስለሆነም የቃላትን ትክክለኛ ትርጉምና ፍቺ ማወቅ ለሰው ልጅ አንድነትና መግባባት፣ እንዲሁም ለቋንቋ ባለቤትነት መሟላት መሠረት መሆኑ ግልጽ ነው። ቋንቋም ሆነ ቃላት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከህብረተሰቡ ታሪካዊ እድገት ጋር መለወጣቸው የማይቀር ነው። እርግጥ ነው፣ ብዙ ቃላት ሳይለወጡ ዘመናት ያልፋሉ። እነዚህ ቃላት ብዙውን ጊዜ የተፈጥሮን ባህርይና ሀይሎች የሚያመለክቱ ናቸው የዩኒቨርሲቲ መምህራን የውይይት ማህበር (1980፣7-8)።

እንደ እንግዳው (1993፣16) አገላለጽ፣ ቃል የትርጉም መጀመሪያ ነው። ቃላት ለነገሮች፣ ለሃሳቦች፣ ለስሜቶች፣ ለፍጡራን እና ለመሳሰሉት ስያሜ ወይም መጠሪያ ሆነው ያገለግላሉ። ከቋንቋ አወቃቀሮች ውስጥ የመግባባት መንፈስ የሚጀምረው በቃላት አፈጣጠር ላይ ነው። በሌላ በኩል ባየ (1987) ከምዕላድ ጋር በማያያዝ ሲገልጹ፣ ቃላት ትርጉም ያላቸውና ትንንሽ ሆነው .... በንግግር ክፍሎች ሊመደቡ የሚችሉ የቋንቋ አካላት ናቸው።

ዘሪሁን (1996፣83) እንደሚያብራሩት፣ በሥነ-ጽሑፍ አገባብ ቃላት ከመዝገበ ቃላት መሠረታዊ ትርጉማቸው በተጨማሪ፣ ከሌሎች ቃላት ጋር ሲጣመሩ አዲስ ትርጉም ሊኖራቸው ይችላል። ይህን በመገንዘብ ቃላትን በጥንቃቄ መምረጥ ያስፈልጋል። ይህን ለማድረግ የቃላትን መሠረታዊ ትርጉም (እማሬ) እና ተጨማሪ ትርጉም (ፍካሬ) መገንዘብ ያስፈልጋል። እንዲሁም Garns and Redman (1986), and Harmer (1994) ደግሞ የታላሚ ቋንቋ ተማሪዎች ይኽንን እውቀት እንዲላበሱ ለማድረግ እንዲማሯቸው የሚቀርቡላቸው ቃላት አመራረጥ የተማሪዎች ፍላጎት፣ የቃላት ተጨባጭነት ወይም ረቂቅነትና የድግግሞሽ መጠን ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ።

የአንድ ቃል ፍካሬ እንደሚገኝበት አውድ፣ እንደ ጥንታዊ አገባቡና እንደ ማህበረሰቡ ባህል ይወሰናል። ለምሳሌ ቤት የሚለው ቃል በእማሬው መጠልያን ወይም ሰዎች የሚኖሩበትን፣ ከብርድ፣ ከሙቀት ወይም ከዝናብ የሚጠለሉበትን አንድ አይነት ውቅር ያመላክታል። በፍካሬው ደግሞ እንደየአውዱ ቤተሰብን፣ ትዳርን፣ ምቾትን፣ የሞቀ ኑሮን… ሊጠቁም ይችላል። በአጠቃላይ ቃል ማለት የመዝገበ-ቃል ትርጉም ያለውና ህብረተሰቡ የሚግባባበት ድምጾች ሥርዓታዊ ቅንብር ነው በማለት እንግዳው (1993፣336) ይገልጻሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ትርጓሜዎች መረዳት የሚቻለው ቃላት የተለያዩ ትርጉሞች እንዳሏቸው ነው፤ እንዲሁም የትኛውም ትርጉም መነሻ ቃል እንደሆነ ነው። ከቋንቋ ጥናት አንጻር ስንመለከት ቃላት ከትንንሽ የንግግር ክፍሎች የተገነቡና ወደ ትንንሽ ትርጉም ያላቸው አካላት ሊከፋፈሉ የሚችሉ ናቸው። ከቋንቋ አወቃቀር አንጻር የመግባባት ስሜት የሚጀምረው በቃላት አፈጣጠር እንደሆነ ይታያል። በሥነ-ጽሑፍ አገባብ ደግሞ ቃላት ከሌሎች ቃላት ጋር በመጣመር አዲስ ትርጉም የሚፈጥሩ በመሆኑ፣ ጸሐፊው ቃላትን በጥንቃቄ መምረጥ እንዳለበት ያሳያል። በአጠቃላይ ቃላት መዝገበ-ቃላዊ እና አውዳዊ ትርጉም እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል።

### 2.1.2 የቃላት ትምህርት ምንነት

የቃልን ምንነት በሚመለከት የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን የብያኔ ሀሳብ ሰንዝረዋል። ከነዚህም መካከል Ur (1996, 60) ቃል በጥሬው ሲታይ የተወሰነ ጽንሰ ሀሳብ የሚወክል የድምጾች ቅንጅት ነው። በሌላው McCarthy (1990, 3) እንደሚገልጹትም ቃላት ትርጉም ያላቸውና ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ የቋንቋ አሀዶች ናቸው። እዚህ ላይ ካለው የምሁራን አገላለፅ የምንረዳው ቃል የአንድ ነገር ወካይና ትርጉም መስጠት የሚችል የቋንቋ አሃድ መሆኑን ነው።

በተጨማሪም ባየ (2000፣72-74) በበኩላቸው ስለቃል ምንነትና በቃልና በምዕላድ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት በተመለከተ እንደገለጹት መጀመሪያ ነገር ቃልም እንደምዕላድ ሁሉ ትርጉም አለው። ሁለተኛም ቃል ራሱን ችሎ ስለሚቆም ነፃ ነው። ጥገኛ አይደለም። በዚህ ባህሪው ከነጻ ምዕላድ ጋር ይመደባል። ሶስተኛም ቃል በውስጡ ብዙ ጥገኛ ምዕላዱችን ልይዝ ይችላል። ትርጉም አዘል ወደሆኑ አነስተኛ ክፍልች ሊሸነሽን ይችላል ማለት ነው። በዚህ ባህሪው ደግሞ ከምዕላድ ይለያል። ምክንያቱም ምዕላድ ወደ አነስተኛ ክፍሎች ሊሸነሽን አይችልም ብለናልና በማለት ያብራሩታል።

ዘሪሁን (1996፣83) እንደገለጹት የቃላት ሀሳብን የማስተላለፍ ደረጃና አቅም የተለያየ መሆኑ ግልጽ ነው። ሁሉም ቃላት እኩል የገለጭነትና የስዕላዊነት አቅም አይኖራቸውም። አንደንድ ቃላት ሰፊ ሀሳብን አምቆ የመያዝ ችልታ ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ተራ በመሆናቸው እንዲህ ያለው አቅም ያነሳቸው ሆነው ይገኛሉ። Ur (1996፣60), Lewis and Hill (1985፣98)ን ጠቅሰው እንደሚገልጹት ቃል ከቃል ግንድና ቅጥያ ምዕላድ ብቻ ሳይሆን ከአንድ በላይ በሆኑ ቃላት ጥምረት ሊመሰረት ይችላል። ለምሳሌ /እንጀራ እናት/ የሚለውን ቃል ብንመለከት ከሁለት ምዕላዶች የተገነባ ሲሆን ምዕላዶቹ ራሳቸውን ችለው ሊቆሙ የሚችሉ ቃላት ናቸው። ይሁን እንጂ /እንጀራ እናት/ የሚለው የሁለት ቃላት ቅንጅት የቆመው ለአንድ ነጠላ ፍች በመሆኑ አንድ ቃል ነው። እነዚህ ቃላዊ ሀረጋት ልክ እንደ ነጠላ ቃል ሁሉ በመዝገበ ቃላት ውስጥ በተደጋጋሚ ሊያጋጥሙ ይችላሉ። የአንዳንዳቹ ፍች ከተጣማሪ ቃላቱ ተናጥላዊ ፍች በመነሳት ወድያውኑ ሊታወቅ የሚችል ሲሆን ለምሳሌ(ብረት ምጣድ)፣ የአንዳንዶቹ ደግሞ ከተዋቀሩባቸው ቃላት ነጠላ ፍች በመነሳት ፍቺያቸው ሊደርስበት የማይችል ለምሳሌ (ደጅ-ሰላም) አይነት ይሆናሉ በማለት ይገልጻሉ።

አብይ (1991) River (1981፣24)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት ቃላትን በቀጥታ ተማሪዎችን ማስተማር ተገቢ አይደለም፤ ነገር ግን በተለያዩ መልመጃዎች ውስጥ ነገሮችን በሚያስረዱ መልኩ ቀጥታ ባሌሆነ መንገድ ማስተማር ነው። መምህራን ቃላትን በቀጥታ ከመተርጎም ይልቅ ተማሪዎች የቃልን ትርጉም በምሳሌ፣ በማብራሪያ፣ በፍች፣ በማነፃፀር እንዱሁም ልዩነት በመግለጽ እንደረዱ ማደረግ አስፈላጊ ነው። እላይ ከተገለጸው ማብራሪያ መረደት እንደሚቻለው ተማሪዎች የአንድን ቃል ፍች በቀጥታ የሚማሩ ከሆነ የአንድን ቃል የተለያዩ ፍችዎችን ማወቅ አይችለም፤ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የተማሪዎች የቃላት ችሎታ ዝቅተኛ ይሆናል። ስለዚህ የቃላት የዕውቀት አድማሳቸው እንዲጨምር ቃላትን በምሳሌ ማብራራት አስፈሊጊ መሆኑን ነው።

ምክንያቱም ይህ የትምህርት ዘዴ ከቅርጽ ይልቅ ለትርጉምና ለመስተጋብራዊ ተግባር ትኩረት ስለሚሰጥ፣ ለዚህ ደግሞ የቃላት እውቀት አስፈላጊ በመሆኑ ነው:: ተማሪዎች በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉትን ቃላት በተለያዩ መንገዶች ሊማሩ ይችላሉ:: የመጀመሪያው መንገድ በቋንቋው የመማር ሂደት ውስጥ ከሚያገኟቸው ሰዎችና ከአካባቢያቸው በመደበኛ ባልሆነ መንገድ የሚማሩበት ነው:: ሁለተኛው መንገድ ደግሞ በመደበኛ መንገድ በትምህርት ቤት የሚማሩበት ነው::በመደበኛ መንገድ የሚካሄደው የቃላት ትምህርት፣ አንድ ተማሪ በክፍል ውስጥ ከሚቀርበው የቋንቋ ትምህርት አዳዲስ ቃላትን የሚተዋወቅበት ሂደት ነው::

በአጠቃላይ በዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ውስጥ ቃላት Carter and McCarthy (1988:19) በዝርዝር የገለጿቸው፣ፍች ያላቸውና ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ ነጠላ ቃላት፣ በጥመራ የተመሰረቱ ቃላት፣ ፈሊጣዊ ቃላት (አነጋገሮች) እንዲሁም የተለመዱ አገላለጾች ናቸው::

### 2.1.3 የቃለት ትምህርት አስፈላጊነት

በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ የቃላት እውቀት ትልቅ ሚና ይጫወታል:: በዚህም ምክንያት የቋንቋ ሊቃውንት በቋንቋ ትምህርት ለቃላት ትኩረት መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ:: Gairns and Redman (1986) የቃላት ትምህርት በጣም አስፈላጊ በመሆኑ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሳይዘነጋ መካተት እንዳለበት ይገልጻሉ:: ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍትን የሚያዘጋጁ ሰዎች ቃላትን በይዘትነት በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ማካተት እንዳለባቸው ያሳስባሉ:: በተጨማሪም በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ቃላትን ስናካትት የትኞቹ ቃላት ተማሪዎችን የተሻለ እንደሚያግዙ በመለየት እንዲሁም ያላቸውን ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተመርጠው ቢካተቱ መልካም እንደሆነ ያስረዳሉ::

Wilkins (1972) ሰዋስው ሳይኖር በጣም ጥቂት መልዕክት ማስተላለፍ ይቻላል፤ ነገር ግን ቃላት ሳይኖሩ ምንም ዓይነት መልዕክት ማስተላለፍ አይቻልም በማለት ይገልጻሉ:: ይህ የሚያሳየው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ቃላት ከምንም በላይ አስፈላጊ መሆናቸውን ነው:: በሌላ በኩል የቃላት እውቀት ለማንኛውም የግንኙነት ሂደት አስፈላጊ መሆኑን Nation (2001) ሲገልጹ ሰፋ ያለ ንግግር ወይም መግለጫ የሚጀምረው ከቃላት ነው፤ ትልቅ የሚባል ጽሑፍም የሚመነጨው ከቃላት ነው ይላሉ:: ስለዚህ የቃላት እውቀት አስፈላጊነት አጠያያቂ ጉዳይ አይደለም:: የቃላት እውቀትን ስናነሳ የቃላት ትምህርት አስፈላጊነትም ተነጥሎ የሚታይ ጉዳይ አይደለም በማለት ይገልጻሉ::

የቃላት ትምህርት አስፈላጊነትን በተመለከተ Wallace (1988) በንግግር ወቅት የቃላትን ትክክለኛ አነባብ (ቅላጼ) ለመጠቀም፣ የቃላትን መሠረታዊና ተጨማሪ ትርጉም ለመገንዘብ፣ ቃላትን ከተገቢው ነገርና ጽንሰ ሐሳብ ጋር ለማዛመድ፣ ቃላትን በተገቢው ሰዋስዋዊ ቅርጽ ለመጠቀም፣ የቃላትን ትክክለኛ ዘይቤያዊ አጠቃቀም ለመረዳት፣ የቃላትን የንግግር ወይም የጽሕፈት ቅርጽ ለመለየት እና ቃላትን በተገቢው ደረጃ ለመጠቀም ያስችላል በማለት ይገልጻሉ፡፡

Ur (2009) እንደገለጹት የቃላት ትምህርት የሚከተሉትን ነጥቦች ለማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ እነሱም፦ የቃላትን ትክክለኛ አጠራር (pronunciation) እና አጻጻፍ (spelling) ለማወቅ፣ የቃሉን ሰዋሰዋዊ መዋቅር ለመገንዘብ፣ ቃላት ከሌሎች ቃላት ጋር ያላቸውን አብሮ መጥነት (Collocation) ለመረዳትና የቃላት ፍች በተለያየ አውድ ለመገንዘብ የሚሉት ናቸው፡፡

Gairns and Redman (1986፣65) የቃላት ትምህርት በጣም አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሳይዘነጉ መካተት አለባቸው፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች ቃላትን በይዘትነት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ማካተት እንዳለባቸው ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ ቃላትን ማካተትን ስናስብ የትኞቹን ቃላት ከየትኞቹ በተሻለ የተማሪዎችን ክሂል ያዳብራሉ፡፡ እንዲሁም ካላቸው ጠቀሜታ አንፃር ተመርጠው ቢካተቱ መልካም እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Richards and Rodgers (1995፣24) ቃላት እለት በእለት በምናደርገው አጠቃላይ መስተጋብር ማለትም ሀሳብ መለዋወጥን፣ መልዕክት ማስተላለፍን፣ ጥያቄ ማቅረብንና የመሳሰለትን ነገሮች ለማሳካት የምንጠቀምባቸው ሁለገብ የቋንቋ መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በመናገር፣ በማዳመጥ፣ በማንበብና በመጻፍ ለመግባባት ቃላት ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ ቃላት ሁለተኛ ቋንቋን ለመማር ሁነኛ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ተማሪዎች በቋንቋው የሚፈጥሩት ተግባቦት የጠሩና የቀለጠፈ ይሆን ዘንድ ቃላት ቁልፍ ሚና አላቸው፡፡ በቋንቋ ትምህርት ቃላት ያላቸውን ቁልፍ ሚና እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፡፡

- በንግግር ወቅት የቃላትን ትክክለኛ ቅላፄ እንዲጠቀሙ፣
- የቃላትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች እንዲገነዘቡ፣
- ቃላትን ከሚወክሉት ቁስና ፅንሰ-ሀሳብ ጋር ማዛመድ እንዲችሉ፣
- ቃላትን በተገቢው ሰዋስዋዊ ቅርፅ እንዲጠቀሙባቸው፣

- የቃላትን ትክክለኛ ዘይቤያዊ አጠቃቀም እንዲገነዘቡ፣
- የቃላትን የንግግር ወይም የፅህፈት ቅርፅ ለመለየት፣
- የቃላት ተገቢውን የመደበኛነት ደረጃ ጠብቀው እንዲጠቀሙ ይረዳቿል፡፡

እንግዲህ ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የቃላት ትምህርት ለቋንቋ እውቀት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አላቸው፡፡

የቃላት ትምህርት በውስጡ የተለያዩ ይዘቶችን ያካትታል፡፡ Ur (2009) እንደገለጹት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን የቃላት ቅርፅ (ንበትና አጻጻፍ)፣ የቃላት ሰዋስው፣ የቃላት ክትትሎሽ፣ የቃላት አጠቃቀም (የፍቺ መስፋት)፣ የፍቺ ተዛምዶና የቃላት አመሰራረት በማለት በስድስት ከፍለው ያቀርባሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም Sheldon (1988) አምስት የሚሆኑ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን ዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም፡- የቃላት ቅርፅ፣ የቃላት ንበት፣የቃላት አመሰራረት፣ የቃላት ፍቺና የቃላት አጠቃቀም/አገባብ ናቸው፡፡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች በርካታ ቢሆኑም Wallace (1988) እና ማረው (2003) ጠቅለል አድርገው የቃላት አገባብ፣ የቃላት ፍች፣ የቃላት አጠቃቀምና የቃላት እርባታ/ምስረታ በማለት አስቀምጠዋል፡፡ የሁሉም ምሁራን ሀሳብ ተመሳሳይና እርስ በርሳቸው የሚገናኙ ስለሆኑ እንደሚከተለው ማጠቃለል ይቻላል፡፡ እነሱም፡- የቃላት ፍች፣ የቃላት አገባብ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የቃላት እርባታ/ ምስረታ እና የቃላት ንበት የሚለት ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ቃላት በቋንቋ ለሚከናወን ተግባቦት አስኳል ናቸው፡፡ የቋንቋ ምሁራን እንደሚሉትም በቋንቋ ለመዳ ሂደት ከስነ-አገባብ እውቀት በፊት በቅድሚያ የሚዳብረው የቃላት እውቀት ነው፡፡ ስለዚህም በቋንቋ ትምህርትም መሰረቱ የቃላት ትምህርት መሆን እንዳለበት ለመረዳት አያዳግትም፡፡

### 2.1.4 የቃላት ትምህርት ይዘቶች ማቅረቢያ ስልቶች

የቃላት ትምህርት በመማሪያ መፅሀፍት ውስጥ ማቅረብ የቃላቱን ዝርዝር የማቅረብ ተግባር ብቻ ሳይሆን በተማሪዎች አዕምሮ ውስጥ ሰርፀው በሚቀሩበት ሁኔታ ማዘጋጀትን የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት የተማሪዎችን እድሜ፣ የትምህርት ዳራ፣የትምህርቱን ዓላማ፣ የቃላቱን ባህርይ ያገናዘቡና ቃላቱን በራሳቸው ለመልመድ በሚያስችሉ ስልቶች በዳበሩ መልመጃዎች ላይ የተመሰረቱ ሊሆኑ ይገባቸዋል (Gairns and Redman፣ 1986)፡፡

የቃላት ትምህርት ቃላት እንዴት እንደሚለመዱ እና እንደሚዳብሩ በሚያሳዩ ጠንካራ እሳቤዎች ላይ በመመስረት መቅረብ አለበት በማለት ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ Morgan and Rinvolucri (1986) ቃላት አንድ ነጠላ ትርጉም ብቻ ይዘው የምናገኛቸው ብቻ ሳይሆኑ እርስ በርሳቸው የተሳሰሩ፣ በትስስሯሹ ሳቢያም የተለያዩ ቅርፆችና ፍቺዎችን የሚይዙም ናቸው፡፡ ስለዚህም ተማሪዎች አዳዲሶቹን ቃላት ከቀደመ ዕውቀታቸው ጋር እያገናዘቡ ማሰብና የመተንበይ ችልታቸውን እየተጠቀሙ ቅርፃቸውን ከፍቺያቸው ጋር ማወቅ በሚችሉበት አኳኋን ሊቀርቡ ይገባል በማለት ያብራራሉ፡፡ እነዚሁ ምሁራን ጨምረው እንዳስረዱት የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተነጣጠለ ሳይሆን እንደ ክንውን ቀጥሎ ካለው የተቆራኘና ደረጃ በደረጃ የተዋቀረ ሊሆን ይገባል፡፡ ይኸውም በመጀመሪያ አዳዲስ ቃላት ለተማሪዎች የሚቀርቡበት ሁኔታ ላይ ያተኩራል፡፡ በመቀጠል ተማሪዎች አዳዲሶቹን ቃላት መረዳታቸውን የሚረጋገጥበት ሂደት ይሆናል፡፡

Ur (2009) and Nation (2001) የሚከተለትን የአዳዲስ ቃላት ማቅረቢያ መንገዶች ይዘረዝራሉ፡፡ እነሱም፡- እጥር ምጥን ያለ መዝገበ ቃላዊ ፍች፣ በጥልቀት ማብራራት፣ በተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎችና ድርጊቶች፣ ቃሉ የሚገኝበትን የተለያዩ ዕሁፍች በማቅረብ እንዲገምቱ ማድረግ፣ በተመሳሳይ ፍች፣ በተቃራኒ ፍችና ተያያዥነት ያላቸውን ቃላት በማምጣት የሚሉት ናቸው፡፡

ከላይ ከቀረቡት የምሁራን ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ቃላት በመማሪያ መፅሀፍት ውስጥ ሲቀርቡ የተማሪን የቀደመ እውቀት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ዳራ፣ ወዘተ. ያገናዘቡና ተማሪዎች ቃላቱን በተለያዩ አውዶች በሚያገኟቸው ሁኔታ መሆን እንዳለባቸው የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በቃላት የመማር ስሌቶች ላይ የተካሄደ ጥናቶች በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ዘዳዎችን አስተዋውቀዋል፡፡ ከነዚህ የቃላት ማቅረቢያ ስልቶች መካከል ዋና ዋና የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነሱም፡- ቃላትን በአውድ ማቅረብ፣ ቃላትን በፍች ዝምድናቸው ማቅረብ፣ የቃላት ትምህርትን በመዝገበ ቃላት አስደግፍ ማቅረብ፣ የቃላት ትምህርቱን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ እና ቃላትን ከቋንቋ ክሂልች ጋር በማጣመር ማቅረብ የሚሉት ናቸው፡፡ እነዚህንም እያንዳንዳቸውን ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 2.1.4.1 ቃላትን በአውድ ማቅረብ

አውድን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ይሰጣሉ፡፡ ከነዚህም መካከል Nation and Coady (1988፣102) እንዳሰፈሩት አውድ በአጠቃላይ ገጽታዎች ሊከፋፈልና ሊገለጽ

የሚችል ሆኖ በአንድ በተሰጠ ውህድ አሀድ ውስጥ እንደ ስነ-ምዕላዳዊ፣ ስነ􀀀አገባባዊና ዲስኩራዊ መረጃ ሊታይ ይችላል በማለት ያስረዳሉ፡፡ አያይዘውም የውህድ አሀድ አንባቢ ወይም አድማጭ ውህድ አሀድ ስለሚናገረው ጉዳይ የራሱ የሆነ ዳራዊ ዕውቀት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም አውድ ቋንቋ በጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ የሚያመቻች ሁኔታ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል Lewis (1993፣8) ቃል በቁሙ ከሚሰጠው ትርጉም በተለየ መልኩ በሌሎች ከጎኑ በሚቆሙ ቃላት አማካኝነት ትርጉሙ ተወስኖ የሚቀርብበትን ሁኔታ ይመለከታል፡፡ እንዲሁም አውድ ንግግሩ የተነገረበትን ሁኔታ እና ንግግሩ የተነገረበትን ስነልሳናዊ አካባቢ ያካትታል፡፡ ስለዚህ አውድ ስንል ሁኔታዊ አውድና ስነልሳናዊ አውድ በማለት በሁለት መንገድ ከፍሎ ማየት ይቻላል በማለት ያስረዳሉ፡፡

ከምሁራኑ ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው የአንድን ቃል ፍች መወሰን የሚቻለው ቃል በቀረበበት አውድ ነው፡፡ ይህም አንድ ሰው ለፍርድ ቤትና ለሚወዳት ባለቤቱ አንድን ጉዳይ በተመሳሳይ ቋንቋ አያብራራም፡፡ በሌላ በኩል ሀሳብን በመግለጽ ሂደት ቃላት ብቻቸውን አይከሰቱም፤ በስነልሳናዊ አውድ ታጅበው (ከሌሎች ቃላትና ሀረጋት ጋር አብረው) እንጂ፡፡ ማስተላለፍ ለተፈለገው መልዕክት የተስማሚ ቃል ምርጫም ፍችን በመፍጠር ውስጥ የሚመጣ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ ስነልሳናዊ አውድ ምርጫን በመደገፍ ወይም በመገደብ ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ሁለት ቃላት በአንድ በተወሰነ አውድ ገብተው ተቀራራቢ ፍች ሲያስገኙ ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ናቸው ይባላሉ (ምንውየለት፣ 2005)፡፡ ቃላት ፍፁም ተመሳሳይ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም በፍቺ ተመሳስሎ እንጂ በአውድ አንዱ ቃል ሌላውን ላይተካ ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ Gairns and Redman (1986) እንደገለፁት ሁለት ቃላት ፍፁም የሆነ ተመሳስሎ ቢኖራቸው ኖሮ በቋንቋው ውስጥ የሚኖራቸው ተፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ ይገባ ነበር፡፡

### 2.1.4.2 ቃላትን በፍች ዝምድናቸው አማካኝነት ማቅረብ

McCarthy (1990፣39) ተማሪዎች የቃላትን ንበት መመሳሰል መሰረት አዴድርገው ቃላት ቢያከማቹም፣ በኋላ በትምህርት እየገፉ ሲሄዱ ቃላትን በአዕምሮ ሰሌዳቸው ቀርፀው የሚያስቀምጡት በፍችያቸው አማካኝነት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ እያሉ ቃላትን በዝምድናቸው መነሻነት ማቅረብ በቀላሉ የቃልን ፍች እንዱገነዘቡ ያደርጋል በማለት ያስረዳሉ፡፡ Wilkins (1972፣124) and Bahuer (1998፣31-34) እንደገለፁት ደግሞ፣ ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነውን የቃላት እውቀት ለማስጨበጥ የአዳዲስ ቃላት ፅንሰ

ሀሳባዊና አገልግሎታዊ ልዩነቶችን በሚያሳይ መንገድ ማቅረብ ይገባል፡፡ በመሆኑም Bahuer (1998፣31-34) እንደገለፁት ቃላትን በተመሳስሏቸውና በተቃርኗቸው፣ በቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት እንዱሁም በአብሮ ተሰላፊነታቸው ለይቶ ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡ እነዚህ የቃላት የፍች ዝምድናዎችም ቀጥሎ ባጭር ባጭሩ ቀርበዋል፡፡

## 2.1.4.2.1 ቃላትን በተመሳስሎና በተቃርኖ ፍችያቸው ማቅረብ

በቃላት መካከል በጣም የታወቀው ትስስሮሽ የቃላት በፍች መመሳሰልና መቃረን ነው፡፡ ሁላት ቃላት በአንድ በተወሰነ አውድ ገብተው ተመሳሳይ የሆነ ፍችን ሲያስገኙ ሁለቱ ቃላት ተመሳሳይ ሲባል፣ በአንፃሩ ሁለቱ ቃላት በፍች ተፃራሪ ሆነው ሲገኙ ተቃራኒ ቃላት ይባላሉ፡፡ Allen (1983) በቃላት መካከል ፍፁም የሆነ ተመሳስሎ የለም፡፡ ምክንያቱም ቃላት በፍች ተመሳስሎ ካልሆነ በስተቀር በማንኛውም አውድ አንድ ቃል ሌላውን ሊተካ አይችልም፡፡

እንዲሁም ቃላት በተወሰነ መልኩ የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት መጠነኛ ባህሪ አላቸው፡፡ ይህም ማለት የአንዱ ቃል የሰፋ ፅንሰ ሀሳብ መያዝ፣ አንዱ በገባበት ሌላው አለመግባት፣ ሰዋስዋዊ ባህሪያቸው መለያየት ወዘተ የሚሉት በምክንያትነት ይጠቀሳል፤ በማለት ያስረዳል፡፡ በተያያዘም Gairns and Redman (1986፣23) እንደሚገልጹት ሁለት ቃላት ፍፁም በሆነ ተመሳሳይነት ማገልገል የሚችሉ ቢሆን ኖሮ በቋንቋው ውስጥ የሚኖራቸው ተፈላጊነት አጠያያቂ ይሆን ነበር፤ በማለት ከላይ ያለውን ሀሳብ ያጠናክሩታል፡፡ በሌላ በኩል የቃላትን ተቃርኖ በተመለከተ ደግሞ በአንድ ቋንቋ ውስጥ በቃላት መካከል የተለያዩ የተቃርኖ አይነቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡

አንዳንድ ቃላት በተፈጥሯቸው ወይም ከአገባባቸው በሚያስገኙት ፍች ተፃራሪ ሊሆኑ ይችላሉ፤ እነዚህን ቃላት ተቃራኒ ቃላት እንላቸዋላን፡፡ በቃላት መካከል መመሳሰል እንዳለ ሁሉ መቃረንም ይኖራል፡፡ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት የተለያየ የተቃራኒ አይነት አላቸው፡፡ እንደ Gairns and Redman (1986) ገለፃ የሚከተለት የተቃራኒ አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- የደረጃ ተቃርኖ፣ አቅጣጫ ጠቀስ ተቃርኖ፣ የተገላብጦሽ ተቃርኖና የተፃራሪ ተቃርኖ ናቸው፡፡

## 2.1.4.2.2 የቃላት የከታች ተከታች ግንኙነት

ከፍች አንፃር የቃላት ዝምድና የሚገለጽበት ሌላው መንገድ የቃላት ተዋረዳዊ ቁርኝት ነው፡፡ አንድ ቃል ሰፊ ያለ ፅንሰ ሀሳብ በመወከል የተነሳ በስሩ በርካታ ቃላት የሚኖራቸውን ፍች ሊያቅፍ ይችላል፡፡ ይህንን የአንድ ቃል ፍች በሌላ ቃል ፍች የሚጠቃለል ሆኖ ሲገኝ የሁሉቱ ቃላት ዝምድና የከታችነትና የተከታችነት የፍች ግንኙነትን ያመለክታል፡፡ ይህን ሁኔታ በምሳሌ

ስናየው፣ ተክል የሚለው ቃል በስሩ ፍራፍሬ፣ የምግብ ሰብለችን፣ አበባ፣ ዛፍ የሚሉ ቃላትን ፍቺ መጠቅለል ይችላል። እነዚህ ቃላት በተራቸው በስራቸው ሌሎች ቃላትን ሊያቅፉ ይችላሉ። ተክል የሚለው ቃል ከታች ቃል ሲሆን የቀሩት (ፍራፍሬ፣ የምግብ ሰብል፣ አበባና ዛፍ) እያንዳንዳቸው ተክል በሚለው ቃል ውስጥ ተከታች ናቸው። እርስ በርሳቸው ያላቸው ግንኙነት ደግሞ የአብሮ ተከታችነት ግንኙነት ነው። ሁለቱ ቃላት አብሮ ተከታች ሊባሉ የሚችሉት አንድ ለሁለቱም የበላይ የሆነ የጋራ ከታች ቃል የሚኖራቸው ከሆነ ነው፡

ስለከታች ተከታች ቃላት የፍች ዝምድና ሲነሳ፣ አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ያለው የፍች ዝምድና የሚታየው በስሞች መካከል ነው። ይሁን እንጂ ልክ እንደ ቃላት ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍች ትምህርት ሁሉ ፍችን መሠረት ያደረገ የቃላት ትምህርት ተደራጅቶ ከሚቀርብባቸው ስልቶች አንዱ ነው (Carter and McCarthy 1988፣26-27)።

### 2.1.4.2.3 የቃላት አብሮ ተሰላፊነት

በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ቃላት እርስ በርስ ከሚገናኙባቸው ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ የቃላት አብሮ መምጣት (Collocation) ነው። ይህ የቃላት ዝምድና ዓይነት የቃላትን አብሮ ተሰልፉነት ያሳያል። በመሆኑም ይህ ባህሪይ ቃላት አብረዋቸው ከሚቀናጁ ቃላት ጋር በመሆን ሰፋ ያለ ፍች እንዲያስገኙ ያደርጋል። የቃላት አብሮ የመሰለፍ ሁኔታ በማንኛውም የቋንቋ ጥናት ሂደት ውስጥ ዋና የቃላት አደራጅቶ መቅረቢያ መንገድ ነው። ይህ ባህሪይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቃሉን እንዲይዙና የተለያዩ የፍች አካባቢዎችን እንዲረዱ ያግዛል።

### 2.1.4.2.4 ቃላትን የእርባታና የምስረታ ስርዓት መሰረት አድርጎ ማቅረብ

Ur (1996፣62) እንደሚገልጹት የቃላት ትምህርት ማቅረቢያው ሌላው ስሌት የጎላ ጠቀሜታ እንዳላውቸው የሚታመንባቸው ቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደታቸውን በመከተል ማቅረብ ነው። በቋንቋ ውስጥ በአንጻራዊ አነጋገር ጥቂት ቁጥር ያላቸውን የቃላት አፈጣጠር ሂደቶች በመከተል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላትን መፍጠር ይቻላል። ቃላት የተለያዩ አርቢ ምዕላዶችን በመጨመር ልዩ ልዩ ቅርፆች ሊይዙ ይችላሉ።

እንደ ጌታሁን (1990፣50) አገላለፅ፣ በአማርኛ ቋንቋ ቅጥያዎች ቃላትን የማርባትና የመመስረት ተግባር አላቸው። የእርባታ ሂደት የቃሉ መሠረታዊ ባህርይ ሳይለወጥ በቅጥያዎች አማካኝነት የሚደረግ የቃላት የእርባታ ሂደት ሲሆን በቅጥያ አማካኝነት ከነበሩበት የቃል ክፍል ወደ ሌላ የቃል ክፍል የሚለዋወጡበት ሂደት ደግሞ ምስረታ ይባላል። በተያያዘም ባየ (2000፣108-109)

እንደሚገልጹት በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ ቃላትን ለማርባትና ለመመስረት የሚያስችል የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ቅጥያዎች አሉ።

### 2.1.4.2.4 ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

Morgan and Reinvlucri (1986) የተማሪዎችን የቃላት ዕውቀት ከፍ ለማድረግ ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለው ከዘረዘሯቸው የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ መንገዶች አንዱ ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ነው። በሌላ በኩል Gairns and Redman (1986) እንደገለጹት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የመዝገበ ቃላት አጠቃቀም የማይቀር የማንኛውም መርሃ ትምህርት አካል ነው። እነዚሁ ምሁራን አያይዘው እንደሚያስረዱት የአንድ ቋንቋ የቃላት ትምህርት በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ ተማሪዎች የቃሉን የተለያየ ፍቺ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። ተማሪዎች ከክፍል ውጭ መምህራቸውን ወይም ጓደኞቻቸውን ጠይቀው መረዳት በማይችሉበት ሁኔታ መዝገበ ቃላትን ተጠቅመው የቃሉን ፍቺ ሊረዱ ይችላሉ። ሶስት ዓይነት መዝገበ ቃላት እንዳሉ Seal (1991) ይገልጻሉ። የመጀመሪያው ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት ነው። ይህ መዝገበ ቃላት የታለሚውን ቋንቋ ቃላት በተማሪው አፍ መፍቻ ቋንቋ ቃላት ይተረጉማል። ሁለተኛው ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት ሲሆን የታለሚውን ቋንቋ ቃላት በዚያው በራሱ የሚፈታ መዝገበ ቃላት ነው። ሶስተኛው መደበኛ መዝገበ ቃላት ሲሆን በአንድ ቋንቋ የሚዘጋጅና አፍ መፍቻንም ኢ-አፍ መፍቻንም ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መዝገበ ቃላት ነው። ከላይ ከተዘረዘሩት የመዝገበ ቃላት ዓይነቶች ውስጥ ቋንቋውን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በይበልጥ የተሻለ የሚሆነው ልሳነ-ክልኤ መዝገበ ቃላት ነው። ምክንያቱም ኢ-አፍ መፍቻ ተማሪዎች ቃላቱን በራሳቸው አፍ መፍቻ ተብራርተው (ተተርጉመው) ስለሚያገኟቸው በቀላሉ ያለ አጋዥ ሊረዱ ይችላሉ። ስለዚህ የሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍት ሲዘጋጁ ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላትን የመጠቀምንም ብልሃት ቢያካትቱ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት ይጠቅማቸዋል። በመሆኑም መማሪያ መጻሕፍት የመዝገበ ቃላቱን የአጠቃቀም ዘዴንም ጭምር ሊያካትቱ ይገባል።

### 2.1.4.2.5 የቃላት ትምህርትን ግልጽ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ

ተማሪዎች የሚጠበቀውን የችሎታ መጠን፣ አመለካከትና የባህሪይ ለውጥ እንዲያመጡ ከተፈለገ የቋንቋ መለመጃ መመሪያዎች ቋንቋ ነክ ተግባራትን የሚያካትቱና ተማሪዎችን ለልምምድ የሚጋብዙ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል (Nation, 2001)። በተጨማሪም Wallace (1988) እንደጠቆሙት ግልጽና በማብራሪያ የተደገፈ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ለማዘጋጀት በቃላት

ትምህርት ዙሪያ የተሰሩ የጥናት ውጤቶችን ማየት አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ተመሳሳይ ቃላትን ለማስተማር የተዘጋጁ መመሪያዎች የቃላትን የተመሳሳይነት/ልዩነት መጠንን የሚጠቁሙ ማብራሪያዎችም ቢጨመሩባቸው ተማሪዎች የቀረቡላቸውን መልመጃዎች በተፈለገው መጠን ሊሰሩ ይችላሉ።

በአጠቃላይ የቃላት ትምህርት የመልመጃ መመሪያዎች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ሲዘጋጁ የመመሪያው ትኩረት አቅጣጫ፣ መልመጃው ያተኮረበትን ይዘትና ምሳሌዎችን በአግባቡ የያዙ መሆን አለባቸው። በተጨማሪም መመሪያዎቹ ለተማሪዎች ግልጽ፣ የተብራሩ፣ ጾታን በአግባቡ የሚገልጹና በጥንቃቄ የተቀረጹ መሆን ይኖርባቸዋል።

### 2.1.4.2.6 ቃላትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማጣመር ማቅረብ

ተማሪዎች የተረዷቸውን አዳዲስ ቃላት አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ መጠቀም የሚጀምሩት የቅበላ ክሂሎቻቸውን ተጠቅመው ባገኙት እውቀት ነው። Lewis (1993፣ 114) እንደሚገልጹት መግባባት እንዲችሉ በተገቢ ሁኔታ በቃላት ትምህርት መታገዝ ይኖርባቸዋል። በመሆኑም ቃላትን ከሌሎች ክሂሎች ጋር አጣምሮ ማቅረብ የመማር ሂደቱን የተቃና ያደርገዋል። ይህም የተማሪዎች የተግባቦት አቅም መጠኑን በጠበቀ የቃላት ትምህርት ክንውን እንዲታገዝ ያደርጋል።

### 2.1.4.2.7 ቃላዊ ሀረጎችን ለመረዳት በሚያስችል ስልት ማቅረብ

Lewis (1993፣98) እንደሚገለፁት የቃላት ትምህርት ትኩረት ነጠላ የሆኑ ቃላትን ብቻ ሳይሆን ረጅምና ባለብዙ ሀረጎችንም ማካተት አለበት። በመሆኑም የቃላት ትምህርት ቃላዊ ሀረጋትን በቃላት ትምህርት ውስጥ ማካተት ከቻለ ተማሪዎች በቋንቋው በሚገባ ለመግባባት እንዲችሉ ከማገዝ አንፃር ትልቅ ድርሻ አለው። ቃላዊ ሀረጎችን በቃላት ትምህርቱ ማካተትና ማቅረብ ተማሪዎች በሚያጋጥማቸው የተግባቦት አውድ አንደበተ ርቱዕ ሆነው አላማቸውን ከግብ ለማዱረስ የሚያስችለቸውን መሳሪያ ያስታጥቃቸዋል፤ በማለት ያስረዳሉ። እንዲሁም ብዙ የቋንቋ ብቃት ትዎሪዎች የሚጠቁሙት ቃላት በትውስታ ማህደር የሚቀመጡት ነጠላ ሆነው ብቻ ሳይሆን የሀረግ አካል ሆነው ጭምር እንደሆነ ያብራራሉ።

በአጠቃላይ ምሁራን በዝርዝር የገለጿቸው ቃላዊ ሀረጎች፡- በተለያዩ እርባታና የምስረታ ቅጥያ ምዕላዶች የተመሰረቱና የረቡ ቃላት፣ በጥመራ የተመሰረቱ ቃላት፣ ፈሊጣዊ ቃላት (አነጋገሮች) እንዲሁም የተለመዱ አገላለጾች ናቸው።

### 2.1.5 የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ

በቋንቋ እውቀት ውስጥ የቃላት ሚና የላቀ ይሁን እንጂ የአንዱን ቋንቋ ቃላት በአንድ ጊዜና ቦታ ሁሉንም አቅርቦ ማስጠናት ስለማይቻል መምረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይም በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ለማቅረብ መምረጥ አስፈላሊጊ እንደሆነ አጠያያቂ አይደለም፤ አመራረጡ ላይ እንጂ፡፡ አመራረጡን በተመለከተ Hutchinson and Torres (1994) በመማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ሂደት ውስጥ የትኞቹ ቃላት ለተማሪዎች በመሰረታዊነት እንደሚያስፈልጉ መወሰን ዋና ጉዳይ ነው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከላይ መረዳት እንደሚቻለው መማሪያ መጻህፍት በሚዘጋጁበት ጊዜ ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን መወሰንና መለየት አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን አንድ የሚነሳ ጥያቄ አለ ይህም ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ቃላትን እንዴት እንምረጣቸው የሚለው ነው፡፡ይህንንም Dubin and Olshtain (1986) በቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ ስለሚካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ሲነሳ ለተማሪዎች ባላቸው ጠቀሜታ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ቃላት እንዴት ይመረጡ? የሚለው አብይ ጥያቄ ነው፡፡ የስነ-ልሳን ምሁራንም ለጥያቄው ምላሽ የሚሆን የቃላት መምረጫ መስፈርት ለማዘጋጀት ለበርካታ አመታት የተለያዩ ሙከራዎችን አድርገዋል በማለት ያጠናክሩታል፡፡ ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት ከሞከሩት መካከልም www.ccsenet.org. vol.3, No.3 (2010) ላይ እንደሰፈረው የቃላትን ትምህርት ለእለት ተእለት መግባቢያነት በሚያገለግሉ ቃላት መጀመር ያስፈልጋል፡፡ ይህም ቀስ በቀስ የቃላትን የአገልግሎት ደረጃና ተገቢነት ተከትሎ ለማስተማር ያግዛል በማለት ያብራራሉ፡፡

ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን ከአስፈላጊነታቸው በመነሳት መምረጥ እንዳለብንና ልንከተላቸው ስለሚገቡ መስፈርቶች የተለያዩ ምሁራን የሚዘረዝሯቸው ነጥቦች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል Gairns and Redman (1986፣57-64) የተማሪውን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ፣ የቃላት የድግግሞሽ መጠንን፣ የቃላት የፍቺ ሽፋን፣ የቃሉ ተስተማሪነት፣ እና ባህላዊ ተላውጥን መሰረት ያደርጋል፡፡ እነሱም እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

#### 2.1.5.1. የተማሪውን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ

ተማሪ እንዲማር የሚቀርቡለት ቃላት ሲመረጡ ሊስተዋሉ ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ አንዱ ነው፡፡ McCarthy (1990፣69) የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ የተማሪውን ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃና የቀድሞውን እውቀት ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡ እንዲሁም Atkins and Etal (1996፣33) ሲያስረዱ የመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች ቃላትን ለመምረጥ ሲነሱ በመምህራን የተካሄዱ የተማሪዎች ፍላጎት አሰሳዎችን፣

በግል ደረጃ እያንዳንዱ ተማሪ ይኖረዋል ተብሎ የሚታሰበውን ፍላጎትን በመተንበይ ማካተት እንደሚኖርባቸው ያስረዳሉ፡፡

Allen (1983፣108) የተማሪውን ፍላጎት የመተንበይ ተግባር ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ በመፈለግ ሊከናወን እንደሚችል ይታመናል፡፡ ጥያቄዎቹም ተማሪዎች በአካባቢያቸው ስላሉ ሰዎች፣ ስለነገሮችና ስለክስተቶች መናገር እንዲችሉ የትኞቹ ቃላት ያስፈልጓቸዋል? ሲማሩ በተደጋጋሚ ለሚያጋጥሟቸው መመሪያዎች ምላሽ መስጠት እንዱችሉ የትኞቹን ቃላት ማወቅ ይኖርባቸዋል? የተወሰነ አካዳሚያዊ ብቃታቸውን ለማሟሊት የትኞቹን ቃላት ማወቅ ያስፈልጋቸዋል? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመመለስ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተማሪዎችን ፍላጎት በመተንበይ በቃላት መረጣው ለማካተት እንደሚቻል ይታመናል በማለት ያብራራሉ፡፡

## 2.1.5.2. የቃላት የፍች ሽፋን

Lewis (1993) እንደሚገልጹት በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ፍችን በማስተላለፍ በኩል እኩል የአገልግሎት ሽፋን የላቸውም፡፡ አንድንድ ቃላት በርካታ ፍችን መሸከም በመቻላቸው በተለያዩ አውዶች ሰፋ ያለ ፍችን ያስተላልፋሉ፡፡ በርካታ ፍችን መሸከም የሚችሉ ቃላት በተለያዩ አውዶች በስፋት ተገኝተው መልዕክት ማስተላለፍ ሲችሉ ጠባብ ፍች ያላቸው ደግሞ ሰፊ ፍች ባላቸው ቃላት ይተካሉ፡፡ ከዚህ አንጻር Wallace (1988፣18-19) እንደሚገልጹት አንዳንድ ቃላት ሰፊ ፍች ስላላቸው ሀሳብን አምቀው መያዝ ችልታ ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ጠባብ ፍች ስላላቸው ሰፊ ፍች ባላቸው ቃላት ስር ይጠቃለላሉ፡፡ በመሆኑም ቃላት ከሚሰጡት ትርጉም አንጻር እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ይኖራቸዋል፡፡ ሰፊ ፍች ያላቸው ቃላት ምስጢርን አምቆ የመያዝ፣ ለአድማጭ ወይም ለአንባቢ የተለየ ትርጉም የመስጠት ባህሪያቸው ፍካሬያዊ ትርጉም ሲሆን ምንም ስውር ትርጉም ሳይኖራቸው ለአዴማጭ ወይም ለአንባቢ ሁሉ የጋራ የሆነ ግልፅ ትርጉም የመስጠት ባህሪያቸው ደግሞ እማሬያዊ ትርጉም ይባላል፡፡ እንዲህ ያለ ሁለት ፍች ያላቸው ቃላት የሚኖራቸው የአገልግሎት ሽፋን ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህ በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ተግባቦታዊ አውድ ውስጥ ተደጋግመው የሚከሰቱና ሰፊ የፍች ሽፋን ያላቸው ቃላት በቃላት ትምህርት ይዘትነት ተመርጠው ሊካተቱ ይገባል፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች የምንረዳው ቃላት ለትምህርትነት በሚመረጡበት ጊዜ በመስፈርትነት የምንከተላቸው ነጥቦችን ነው፡፡

### 2.1.5.3. የቃላት የድግግሞሽ መጠን

Nunan (1991፣118) ድግግሞሽ በውህድ አሀድ ስብስቦች ላይ ያተኮረ የቃላት አጠቃቀም ጥናትን መሠረት በማድረግ በጣም ተደጋግመው የተከሰቱ ቃላትን መለየት የሚቻልበት ስልት ነው፡፡ የማስተማሪያ መፃህፍት ሲዘጋጁም የቃላት ትምህርት ይዘታቸውን ለመወሰን አንዱ ጠቃሚ መስፈርት በመሆን ያገለግላል፤ በማለት ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም በዕለት ከዕለት ተግባቦት ሂደት የሚያገለግሉ ተዘውታሪ ቃላትን ለይቶ ማስተማር ተማሪዎችን በቋንቋ ለመጠቀም የሚያስችል ውጤታማ የማስተማር ስልት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ McCarthy (1990፣66) በማንኛውም ቋንቋ በአጠቃቀም እጅግ በጣም ተደጋግመው የሚከሰቱ ቃላት ለዚያ ቋንቋ ጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ለማሳደግ ተዘውታሪ ቃላትን አስቀድሞ ማስተማር ወሳኝ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ እንደ McCarten (2007፣4) ገለፃ፣ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚቀርቡ ቃላት ተዘውታሪ ቃላት ሊሆኑ ይገባል፡፡ ተዘውታሪ ቃላትን መርጦ ቅደም ተከተላቸውን ለመወሰን በዕለት ከዕለት በሚደረግ ተግባቦት ያላቸውን የድግግሞሽ መጠን ዝርዝር (word list) አዘጋጅቶ መወሰን ይቻላል፤ በማለት ያስረዳሉ፡፡ አያይዘውም የአሀድ ስብስብ ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላትን በመምረጥ ረገድ የትኞቹ ቃላት ወይም የተለመደ አገላለፆች ተዘውታሪ እንደሆኑ የንግግርና የጽሁፍ ቃላትን ለመለየት፣ የቃላትን አውዳዊ አጠቃቀምና የጠበቀ ቁርኝት ያላቸውን ቃላት ለመለየት ያስችላል በማለት ያስረዳሉ፡፡

Nunan (1991፣119) ቋንቋን ለአጠቃላይ ዓላማ ማስተማር ሲፈለግ ተዘውታሪ ቃላትን በድግግሞሽ ቆጠራ ላይ ተመርኩዞ መምረጥ ተገቢ ሲሆን፣ ተፅዕኖ የሚያደርሱ ተላውጦችን በመቆጣጠር ከተከናወነም የቆጠራው ውጤት ከጠቃሚነት ጋር አዎንታዊ የሆነ ግንኙነት ይኖረዋል፣ በማለት ያስረዳሉ፡፡ በድግግሞሽ ቆጠራ ውጤት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩና በርከት ያለ ተለውጦች እንዳለ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ከነዚህም መካከል McCarthy (1990፣ 66-68)፣ Gairns and Redman (1986፣ 55-59) የሚከተሉትን ይዘረዝራሉ፡፡

ሀ. የድግግሞሽ ቆጠራው የተካሄደበት የውህድ አሀድ ስብስብ መጠን፡- የስብስቡ መጠን መብዛት ውጤቱን በማስተማመን ረገድ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

ለ. የውህድ አሀድ ስብስቡ ከፅሁፍ፣ ከንግግር ወይም ከሁለቱም መገኘቱ፡- ስብስቡ ከፅሁፍ ብቻ ሳይሆን ከንግግርም የተወሰደ ቢሆን ይመረጣል፡፡

ሐ. ቆጠራው የአንድ ቃል የተለያዩ እርባታዎች እንደ አንደ ቃል አለመመልከቱ፡- የአንድን ቃል የተለያዩ እርባታዎች ነጣጥሎ መመልከት ሰፋ ያለ መረጃን እንደሚሰጥ ይታመናል፡፡

መ. የውህድ አሀድ ስብስቡ የተቀናበረበት የጊዜ ርዝማኔ፡- የውህድ አሀድ የተጻፈበት ወይም የተነገረበት የጊዜ ርዝማኔ የራሱ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

ረ. ተቆጣሪው የውህድ አሀድ ስብስብ ያካተታቸው የውህድ አሀድ አይነቶችን፣ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች፣ ወዘተ መጠን፡- ይህ ስብስቡ ሁሉንም የውህድ አሀድ አይነቶችን፣ የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ የተለያዩ ስርዓተ አባባሎችን ወዘተ አካቶ መያዝን ይመለከታል፡፡

ሠ. ቆጠራው ተደጋጋሚ የሆኑ ቃላዊ ሀረጎችን መጠቅለል አለመጠቅለሉ፡- በንግግርም ሆነ በጽሁፍ ውስጥ ቃላዊ ሀረጎች (ድርብ ቃላት፣ በቃላት ጥምረት የሚፈጠሩ ፈሊጦች የተለመደ ውስን አገላለፆች) በተደጋጋሚ ያጋጥማሉ፡፡ ስለዚህም ቆጠራው እነዚህንና ከአንድ ቃል ጋር አብሮ የሚሰለፉ ቃላትን ድግግሞሽ ይመለከታል፡፡

### 2.1.5.4. ባህላዊ ተላውጦ

አንድ ህዝብ የራሱ ባህል በተመለከተ የተለየ እውቀት እንዲኖረው ይሻል፡፡ እዚህ ላይ ባህል ሲባል የአንድን ህዝብ የተለያዩ የአኗኗር ባህርይ ማለት ነው፡፡ ይህም የህዝቡን ተዋረዳዊ አደረጃጀት (ዕድሩን፣ ደቦውን፣ አስተዳደራዊ ድልድሉን፣ ወዘተ)፣ ተቋማቱን፣ ህጉን፣ ልማዱን፣ ሥራውን፣ ስነ-ጥበቡን፣ ሀይማኖቱን፣ ጨዋታውንና የመሳሰለትን- በአጠቃላይ እሱነቱን የያዘ ነው፡፡ የአንድ ህዝብ የትምህርት ስርዓትም እያንዳንድ ግለሰብ ይህን አጠቃላይ ባህልን የሚያውቅበትንና የሚያደንቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡ ይህ ለተማሪዎች በራስ የመተማመን ደረጃ በማሳደግ የባህላቸውን ምንነት ለመገምገምና ለመረዳት ያግዛቸዋል፡፡ በድሉ ዋቅጅራ (1996፣8) በተጨማሪም መማሪያ መጽሀፍ ሲዘጋጅ በመማሪያ ክፍሉ ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የተለያየ ባህል ካልቸው የህብረተሰብ ክፍል እንደመምጣታቸው መጠን ከባህላዊ አድልኦ (Cultural bias) ነጻ ሆኖ መዘጋጀት እንዳለበት Sheldon, L.E. (1988፣242) ያስረዳሉ፡፡ እላይ ከተገለጸው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ቃላት ተመርጠው በመማሪያ መጽሀፍ ለትምህርትነት ሲቀርቡ የተማሪዎቹን ባህል መሠረት አድርገው መሆን እንዳለበት ነው፡፡ በአጠቃላይ የቃላት ትምህርት በጣም አስፈላጊ እንደመሆኑ መጠን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሳይዘነጉ መካተት አለባቸው፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆችም ቃላትን ለይዘትነት በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ማካተት እንዲለባቸው ምሁራን ይጠቁማሉ፡፡ በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ ቃላትን ለማካተት ስናስብ የትኞቹን ቃላት ከየትኞቹ በተሻለ የተማሪዎችን ክሂል ያዳብራሉ ብለን መምረጥ ይጠበቅብናል፡፡

### 2.1.5.5. የቃሉ ተስተማሪነት

ለማስተማሪያነት የሚቀርበው የቃላት ትምህርት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያጎለብት መሆን አለበት፡፡ የከባድ ቃላት መብዛት በተማሪው ላይ ስነ ልሳናዊና ባህላዊ ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በአንዳንድ ዓረፍተነገር ውስጥ ቀደም ብሎ የማያውቃቸው አዳዲስ ቃላት የበረከቱ እንደሆነ፣ የተማሪዎች ትኩረት በሚያነቡት አጠቃላይ ስራ ላይ እንዳያርፍ እንቅፋት ይሆናል፡፡ የመማር ፍላጎትንም ይቀንሳል፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎት መያዝ የሚቻለው ከተማሪዎች ችልታ እጅግም ባልበለጠ ቃላት የተጻፈ ስራ የተመረጠ እንደሆነ ነው፡፡ አብዛኞቹ የቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍት ለየቀረቡበት የክፍል ደረጃ ይመጥናል ተብለው የተዘጋጁ ምንባቦችን የያዙ ናቸው፡፡ አዘጋጆች በዚያ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን ዕድሜና የቋንቋ ችልታ አጢነው ምንባቦችን ያሰናዳሉ፡፡ ሆነ ተብሎ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጁ ምንባቦች ግን ከህሳቡ በበለጠ (ቢያንስ በእኩል ደረጃ) ቃል መረጣና አረፍተነገር ግንባታ ላይ ያተኩራሉ፡፡ በድሉ ዋቅጅራ (1996፣12 እና 16) እላይ ከተገለጹት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው ለቋንቋ ትምህርት የሚመረጡት ቃላት፤ ለየቀረቡበት የክፍል ደረጃ መመጠናቸው፣ የተማሪዎቹን ዳራና ፍላጎት መሠረት ያደረጉ፣ በአጠቃላይ የቃላት ትምህርትን ተግባራዊ ለማድረግ ምን ያህል ምቹ ናቸው የሚለውን ነው፡፡

### 2.1.6. የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀት

ቃላትን በመምረጥ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ማካተቱ ብቻ በራሱ ለቃላት ትምህርት በቂ አይሆንም፡፡ የተመረጡ ቃላት በተለያየ መልኩ ካልተደራጁ በቀላሉ ተስተማሪ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይህ በእንዲህ እንደለ ለቋንቋ ትምህርትነት የሚውሉ ቃላት በመምረጫ መስፈርት መመረጥ እንዳለባቸው በርካታ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ከላይ የተመረጡት ቃላት በምን መንገድ መደራጀት እንዳለባቸው በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን፡፡ Dubin and Olshtain (1986፣46-47) እንደሚያስረዱት አደረጃጀትን የተመለከቱ የአዳዲስ ርዕሰ ጉዳዮች አቀራረብ፣ ክትትሎሽና መጠነ ርዕይ ውሳኔዎች የሚመሰረቱት በስነ-ትምህርታዊ ስነ-ልሳናዊ እሳቤዎች እንዲሁም በሚኖረው የመማር ማስተማር ሂደት ግንዛቤ ላይ ይሆናል፡፡ እነዚህንም በተመለከተ ምንውየለት (2005፣12) የሺጥላ (1997፣16)ን ጠቅሰው እንደሚገልጹት በስነ-ልሳናዊ እሳቤዎች መሰረት ብዙውን ጊዜ ቋንቋ ከተነጣጠሉ ቅንጣቶች (ቃላት፣ ሀረጋት፣ ዓረፍተ ነገሮች) የተገነባ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም የተነጣጠሉት ቅንጣቶች በጥንቃቄ በሚታቀዱ ተከታታይ ደረጃዎች ተስማሚ በሚሆኑበት ስልት ይደራጃሉ፡፡ በሌላ አንጻር የመማር ንድፈ ሀሳቦች

የትምህርቱ ክትትሎሽና እድገት ከቀላል የቋንቋ ቅርጾች ወደ ከባድ ቅርጾች፣ በጣም በተደጋጋሚ በአገልግሎት ላይ ከሚውሉ ቅርጾች አነስተኛ ድግግሞሽ ወዳላቸው ቅርጾች፣ ተዘወታሪ ከሆኑት ቅርጾች ተዘወታሪ ወዳልሆኑት የሚሄድ አደረጃጀት ሊኖረው እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ አሀዶች እድገታቸውን ጠብቀው በትምህርቱ ሊሸፈኑ ይገባል፤ ይህም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የቋንቋ አሀዶች እድገት ባለው አካሄድ፣ ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ እንዲማሩ በሚያስችላቸው ሁኔታ፣ የቃላት ትምህርት ማስታወስን የሚፈለግ መሆኑን ባገናዘበ መንገድ፣ በተወሰነ በጊዜ ርቀት በመደጋገምና በተለያዩ አውዶች ለመማር ዕድል በሚሰጥ መንገድ መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም ሌላ ቃላት በቋንቋ ክንውኖች ውስጥ የድግግሞሽ መጠናቸውና እድገታቸውን ጠብቀው መደራጀት አለባቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡

McCarthy (1990) እንደሚያስረዱት ቃላትን በተለያዩ አሀዶች ከፋፍሎ ለማቅረብ ከቀላል ወደ ከባድ፣ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳዮች (Topics)፣ በሚኖራቸው የፍቺ ዝምድና እንዲሁም በቅርፅ መመሳሰል ማደራጀት ይቻላል በማለት ያስረዳሉ፡፡ በተያያዘም Aweke (2016) ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላት በመልመጃ ለማዋቀር የቃላቱን የተለያዩ ፍቺ ይዘቶች ስነ□ድምጻዊና ሰዋስዋዊ አወቃቀሮች መሰረት አድርጎ ማቀናጀት ይቻላል፤ በማለት ያስረዳሉ፡፡ እላይ ከተጠቀሱት ማብራሪያዎች መረዳት እንደሚቻለው ቃላትን በመምረጥ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ማካተቱ ብቻ በራሱ ለቃላት ትምህርት በቂ አይሆንም፡፡ የተመረጡ ቃላት በተለያየ መልኩ ካልተደራጁ በመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ቃላት ሲደራጁ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሠረት ቢያደርጉ ይመረጣል በማለት ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

## 2.1.6.1 ከቀላል ወደ ከባድ ማደራጀት

McCarthy (1990፣90) የተመረጡ ቃላት ክብደትና ቅለታቸው ታይቶ ከቀላል ወደ ከባድ በተከታታይ መደራጀት እንዳለባቸው ይገልጻሉ፡፡ የተመረጠው ሁሉ አንድ ጊዜ አይቀርብም፤ቀላሉ ሲቀድም ከባድ ይከተላል በማለት ያስረዳሉ፡፡ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መገንዘብ የሚቻለው በቋንቋ ትመህርት ውስጥ የሚካተቱ ቃላት ሲቀርቡ ደረጃ በደረጃ መሆን እንዳለበት እና ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ ሊገነዘቡት የሚችሉት መሆን እንዳለበት ያመለክተናል፡፡ ይህ ደግሞ ወደ ታለመው ግብ ለመድረስ ቀና መንገድን ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ ቃላትን ለማደራጀት ስንነሳ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከግልጽ ወደ ውስብስብ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከቀዳማዊ ወደ ተከታይ እና ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ በሆነ መንገድ መደራጀት እንዳለባቸው ይመከራል፡፡

እላይ ከተገለጸው ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው ቃላት ከቀላል ወደ ከባድ እያደጉ የሚሄዱ ቢሆኑ ይመረጣሉ፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች ውስብስብ ያልሆነውን በመስራት የሚጠጥርባቸውን ለመስራት እንዲበረታቱ ያስፈልጋል፡፡ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን ሳይጀምሩት ልሰራው አልችልም በሚል ስሜት ሳይሞክሩት ሊቀሩ ይችላሉ፡፡ የዚህ ሁኔታ መከሰት ተማሪዎች በተለያዩ መልመጃዎች በመሳተፍ የቋንቋ ችሎታቸውን እንድያዳብሩ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ይበልጥ ጠጠር ወዳለው ቃላት ከመሄዳቸው በፊት በክብደቱ ቀለል ባለ ቃል ላይ በሚያገኙት ስኬት መበረታታት እንዳለባቸው ነው፡፡ Carter and McCarthy (1988) በማንኛው ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ቃላትን በማደራጀት የማቅረብን ጠቀሜታ ከገለጹ በኃላ ቃላት ሲደራጁ በሁለት ነገር ተከፍለው መሆን አለባቸው ይላሉ፡፡ በተጨማሪም የተማሪው ቃላትን የማወቅ ዕድገት ደረጃ በቃላቱ አደረጃጀት ባህርይ እንደሚወሰን ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም የቃላትን ተከታታይነት በተመለከተ በአንድ የቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የትኞቹ ቃላት ከየትኞቹ ቀድመው መምጣት እንዳለባቸው የሚወሰንበት እና አጠቃላይ የሆነ የቃላት አደረጃጀት ሥራ የሚሠራበት ክፍል ነው፡፡ ይህ ተከታታይነት የቃላቱን የክብደት ደረጃ ከቃላቱ ተደጋግሞ መከሰት ጋር ተያይዞ የሚታይ መሆኑ ነው፡፡

### 2.1.6.2 ቃላት በሚያወሱት ርዕሰ ጉዳይ ማደራጀት

ቃላትን በሚያነሱት ርእሰ ጉዳይ ማደራጀት የራሱ የሆነ ድክመትም ጥንካሬም አለው፡፡ ይህንንም Gairns and Redman (1986፣69) እንደሚገልጹት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ስር ሊጠቃለሉ የሚችሉ ለአንድ ደረጃ የተመረጡ ቃላት የሚያገናኛቸውን ርዕሰ ጉዳይ በመግለጽ እንዲያገለግሉ ከተደረገ በኂላ ቃላቱ በመልመጃ መልክ ተደራጅተው ይቀርባሉ፡፡ በሌላ በኩል McCarthy (1990፣91) እንደሚገልጹት፣ ቃላት በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አደራጅቶ ማቅረብ የራሱ የሆነ ችግር አለው፡፡ ይኸውም ርዕሰ ጉዳይን በተጨባጭ ለመለየት ማስቸገሩ፣ የርዕሰ ጉዳዩን ማወቅ የሚሉትና የመሳሰሉት ከሚያጋጥሙ ችግሮች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ አደራጅቶ የማቅረብ ችግር ቢኖርም ቃላትን አቧድኖ ማቅረብ እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.6.3 ቃላትን በፍች ማደራጀት

Carter and McCarthy (1988፣18) እንደሚገልጹት፣ አንድንድ ቃላት በርካታ የፍቺ አካባቢዎችን ታሳቢ በማድረግ ፍቻቸውን ይዘው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ፍልስፍና፣ ስሜቶችን ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል አንድንዶቹ ደግሞ የሚወክሉትን በቀጥታ ሊጠቁሙ የሚችሉ ጠባብ ፍቺ ያላቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ቀለማት፣ የአናዒ መገልገያ ዕቃዎች ወዘተ መጥቀስ

ይቻላል፡፡ ከዚህም መረዳት የሚቻለው አንድንድ ቃላት ሰፊ ፍቺ ሽፋን ያላቸው መሆኑንና አንድንዶቹ ቃላት ደግሞ ጠባብ ፍቺ ሽፋን እንዳላቸው ነው፡፡

ምንውየለት (2005) የሺጥላ (1997፣18)ን ጠቅሰው እንደሚሉት ቃላት በፍቺ የሚደራጁበት ዋነኛው ምክንያት በፍቺያቸው ተቀራራቢ በመሆናቸው ሳቢያ አንድ የሚመስል ግን መጠነኛ የፍቺ ልዩነት ያላቸው ቃላትን (ለምሳሌ፡- መፅናት፣ መፅናናት) ተማሪዎች እንዲለዩ ማድረግ ነው፡፡ እንዱሁም Gairns and Redman (1986፣69) እንዳሰፈሩት ቃልን በሚገባ ለመረዳት ተማሪዎች ማወቅ ያለባቸው ቃል የሚወክለውን ፍቺ ብቻ ሳይሆን ተዛማጅ ፍቺ ካላቸው ቃላት የሚለየውንም ጭምር ነው፡፡ መጀመሪያ ቃላቱ የሚቀርቡበትን ተገቢ አውድ መፍጠር ይኖርብናል፡፡ ሁለተኛው ከአውዳቸው ፍቺያቸውን ለመገመት የሚያስችል የትንበያ ስልቶችን ከግምት አስገብተው የተማሪዎቹን የመገመት ብቃት ሊያሳድግ በሚችል አኳኋን ትምህርቱን ማደራጀት አለብን፡፡ ስለዚህ ይህንን ታሳቢ በማድረግ ቃላትን ማደራጀት ከቻልን ተማሪዎች በተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው የቃላትን ፍቺ ከአውድ የመረዳት አቅም ያዳብራሉ በማለት ያስረዳሉ፡፡

### 2.1.6.4 ቃላትን በቅርፅ ማደራጀት

McCarthy (1990፣99) ቃላትን ለማስተማር ቃላቱ ያላቸውን ውስጣዊ አደረጃጀት ለማየት በሚያስችል አኳኋን ማደራጀት ሌላው የቃላት ማደራጃ ስልት ነው፡፡ የቃላት አመሰራረት ጥናት ግልፅ እንደሚያደርገው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላት ለመመስረት በመደበኛነት ጥቂት ቁጥር ያላቸው የአመሰራረት ሂደቶች በጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ በመሆኑም የተማሪዎችን የቃላት እውቀት ለማሳደግ የቃላቱን አወቃቀር ስልት ለማሳየት የሚያስችል አደረጃጀት መከተል አስፈላጊ ነው፡፡ ሌላው ትውስታን የተመለከቱ ጥናቶች እንደሚያስረዱት አፍ ፈቶች ቃላትን በአእምሮአቸው በማከማቸት በፈለጉ ጊዜ አስታውሰው የሚመዙበት ሂደት ነው፡፡ ይኸውም ከአእምሮ መደብለ-ቃላት አንዱ ቃል ሲነሳ የሚታወሰው ብቻውን ሳይሆን ከሚመሰርታቸው ሌሎች ምስርትና ድርብ ቃላት ጋር መሆኑ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ ምስርትና ድርብ ቃላትን እንደ አንድ  አሀድ ለመማርና የቃላቱን ምዕላዳዊ አወቃቀር እየበታተኑ ለመመርመር እንዲሁም ፍቺን ከተዋቃሪ ቅርፆች ጋር ለማዛመድ የሚያስችል ቅርፃዊ አደረጃጀት መከተል፣ ለትምህርት የሚቀርቡትን ቃላት ለመረዳትና ለማፍለቅ አስተዋፅኦው የጎላ ነው፡፡

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ በመረጠችው ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሯ በፊት ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸዉን የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዳለች፡፡ በዚህም መሠረት ከዚህ ጥናት ጋር ግንኙነት አላቸዉ ተብለው የታሰቡ ቀደምት ሥራዎችን ለመቃኘት ተሞክሯል፡፡ ጥናታዊ ሥራዎቹ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ሲሆኑ ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥ ጥቂቶቹን ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሞላ (2003) "በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብን መገምገም ነው፡፡ በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በመማሪያ መጽሐፍ የተወሰኑ የቃላት ትምህርት መመሪያዎች በምሳሌና በተብራራ መልኩ ተዘጋጅተው እንዳልቀረቡና ግልጽነት የሚጎድላቸው እንደሆኑ፣ በብዛት ግን በተገቢው ምሳሌዎችና ማብራሪያዎች የተደገፉ መልመጃዎች እንደቀረቡ አመልክቷል፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ከሞላ ጥናት በቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ማተኮራቸው የሚያመሳስላቸው ሲሆን በተተኳሪ መጽሐፍ የታተመበት እንዲሁም ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜ ልዩነት አለው፡፡

ምንውየለት (2005) "በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በአማራ ክልል ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የተዘጋጁ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ መፈተሽ ነው፡፡

በጥናቱ የተገኘው ውጤትም በሁለቱም መማሪያ መጻሕፍት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አብዛኛዎቹ በአውድ ተደግፌው መቅረባቸው፤ቃላቱ ከቀረቡባቸው አረፍተ ነገራዊ አውዶች በአብዛኛው የቃላትን ፍቺ በገቡበት ቦታ ለመገመት የሚያስችሉ አውዳዊ ፍንጮች ይዘው መቅረባቸው፤ይዘት መረጣው ሁሉንም መስፈርት እንዳላሟላ፣ ይሁንና በከፊል እንደተካተተና ይህም በመጻሕፍቱ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሳደረ አመልክቷል፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ከምንውየለት ጥናት ጋር በቃላት ትምህርት ይዘቶች ላይ ማተኮራቸው የሚያመሳስልበት ነጥብ ሲሆን፣ የተተኳሪው መጽሐፍ አዲስ መሆኑና ጥናቱ በተካሄደበት ጊዜና ቦታ ከዚህ ጥናት ጋር በእጅጉ ይለያል፡፡

ሲሳይ (1990) "በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቃላትን የማስተማር ብቃትን መገምገም" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ጥናቱ የ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ የቃላት አቀራረብ በይዘቱ ላይ ሳይሆን በቃላቱ ቅርጽ ላይ ያተኮረ መሆኑን፣ እንዲሁም አውዳዊ አቀራረብን የተከተለ ቢሆንም በአብዛኛው ከአንብቦ መረዳት ጋር የተገናኘ መሆኑን አሳይቷል፡፡ ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም የቃላት አቀራረብ ላይ ትኩረት መስጠታቸው ሲሆን፣ የሚለያየው ደግሞ ይህ ጥናት የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ የሚያተኩር መሆኑ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፣ ጥናቶቹ በተለያዩ ጊዜያት በታተሙ መጻሕፍት ላይ የተደረጉ በመሆናቸው ይለያያሉ፡፡

ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ግንኙነት እንደሚከተለው ነው፡፡ ልዩነቱ የዳንኤል ተክሉ ጥናት አጠቃላይ የትግርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው፡፡

ዳንኤል (1997) በቃላት ክፍሎች በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም ጥናቶች ቃላት ላይ ያተኩሩ መሆናቸው ነው፡፡ ስለዚህ የዳንኤል ጥናት ከቃላት ፅንሰ-ሀሳብ ጋር ተያያዥነት አለው፡፡ በተጨማሪም ጥናቱ በትግርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ሙሉ ያተኮረ ሲሆን፣ይህ ጥናት ደግሞ በ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ይለያያሉ፡፡

በአጠቃላይ፣ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ጥናቶች በነበሩት የመማሪያ መጻሕፍት ላይ የተደረጉ ሲሆን፣ ይህ ጥናት ግን በአዲሱ ሥርዓተ-ትምህርት መሠረት በተዘጋጀው አዲሱ የመማሪያ መጽሐፍ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከቀድሞዎቹ ጥናቶች በእጅጉ የተለየ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት፡ የጥናቱ ዘዴ እና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

## 3.1 የጥናት አይነት

እዚህ ጥናት ከምርምር ዘርፎች መካከል አይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ስለሆነም በመማሪያ መፅሀፉ በቀረቡ የቃላት ትምህርቶች ላይ የቃላት አቀራረብ የይዘት ትንተና (Content Analysis) ተካሂደዋል፡፡ አቀራረቡ ደግሞ ትረካዊ ወይም ገላጭ (Descriptive) ስልት ነው፡፡ ስለዚህ ከሠነድ ፍተሻና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችም በገላጭ (Discribtive) አፃፃፍ ስልት ተተንትነዋል፡፡ ይህ ጥናት ይህን የምርምር ስልት በመጠቀም በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ለመገምገም እንዲሁም የቃላት ትምህርት ይዘቶች በአግባቡ እንዳይቀርቡ የሚያደርጉ ችግሮችን ወይም እንቅፋቶችን መለየት ተችሏል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጭና የናሙና አወሳሰድ

የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲሆኑ በአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ግምገማ በሚለው ርዕስ ጥናት ላይ፣ የሚከተሉት ናሙናዎችና መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪዎች ስራ ላይ ውለዋል፡፡

### 3.2.1 የዞንና የወረዳ ናሙና አመራረጥ

በትግራይ ክልል 6 ዞኖች ቢኖሩም ጥናቱ በደቡባዊ ዞን ብቻ ተወስኗል፡፡ በዚህ ዞን ውስጥ ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል፣ አጥኚዋ በምትሰራው ስራ ምክንያትና ለጥናቷ የሚያስፈልጓት አስፈላጊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አላስፈላጊ ወጪ ለመቀነስ የስለዋ ወረዳ በአመቺ የናሙና (Convenience Sampling) አመራረጥ ዘዴ መርጣለች፡፡ ይህ ናሙና አመራረጥ በዋናነት በወረዳው ከሚሰሩ የአማሪኛ ቋንቋ መምህራን ተጨማሪ መረጃ ለመሰብሰብ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

### 3.2.2 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በተመረጠው የስለዋ ወረዳ ውስጥ 12 እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚያስተምሩ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን፣ አጥኚዋ በዋናነት ከእነዚህ ወዲ ሽረ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለጥናቱ በአመቺ ናሙና (Convenience sampling) መርጣለች፡፡ አጥኚዋ ይህ ትምህርት ቤት እንድትመርጥ ምክንያት የሆናት ከስራ ቦታና ከሚኖር የስራ ጫና የተነሳ ቅርብ በመሆኑ ነው፡፡

### 3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በወረዳው ከሚገኙ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለናሙና የተመረጡት ከሶስት ትምህርት ቤቶች በቁጥር አስር (ሰባት ወንድ እና ሶስት ሴት) ናቸው፡፡ በጠቅላይ ናሙና አመራረጥ ዘዴ (census sampling) ሁሉም የጥናቱ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት በሶስቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰሩ መምህራን በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው ነው፡፡

### 3.2.4 የመማሪያ መጽሀፍ ናሙና አመራረጥ

የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ በዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡ በአላማ ተኮር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያትም የጥናቱ አቅራቢ በዚህ የክፍል ደረጃ መምህር በመሆኗና መፅሀፉ አዲስ በመሆኑ በመገምገም ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን መለየት አስፈሊጊ መሆኑን ስላመነችበት ነው፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ

የዚህ ጥናት ዓለማ በአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበውን የቃላት ይዘት አቀራረብ መገምገም በመሆኑ፣የሰነድ ፍተሻ ዋነኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚህ መሠረት የ2015 ዓ.ም ስራ ላይ የዋለ መማሪያ መፅሐፍ ዋነኛው መረጃ ምንጭ፣ ለስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የተዘጋጁ የቃል መጠይቆች ደግሞ እንደ ተጨማሪ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ሆነው ቀርበዋል፡፡

### 3.3.1. ሰነድ ፍተሻ

የሰነድ ፍተሻ እንደ ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ተደርጎ በዚህ ጥናት ውስጥ ተወስዷል፡፡ ስለዚህ በቅድሚያ እስኪ ስለ ይዘት ትንተና ምንነት የተወሰነ እንበል፡፡ የይዘት ትንተናን በተመለከተ Rebert (1985) የይዘት ትንተና የተለያዩ ጭብጦችን የያዙ ሰነዳዊ መልእክቶች፣ ሀሳቦች፣ ስሜቶች እና አስተያየቶች የሚተነተነባቸውን የተለያዩ ዘዴዎች የሚያቅፍ አጠቃላይ ስያሜ ነው፡፡ እንዲህ ያለ ትንተና በአብዛኛው የተወሰኑ ቃላት፤ ሀረጋት፣ ግብ መቺ ሀሳብ መግለጫዎችና የመሳሰሉት በሰነዱ ውስጥ ስንት ጊዜ እየተደጋገሙ እንደሚመጡ ለማወቅ የሚያስችሉትን ላቅ ያሉ ስሌታዊ ዘዴዎችን ሁሉ ይይዛል፤ በማለት ያብራሩታል፡፡ በሌላ በኩል Koul (1993) እንደሚገልፁት ደግሞ የይዘት ትንተና የመልዕክቱን ወይም የሰነዱን ይዘት በአይነት በአይነት በመመደብና በማስላት ላይ ስለሚያተኩር እንዳንድ ጊዜ ሰነዳዊ፤ መረጃዊና ድርጊታዊ እየተባለ

ይጠቀሳል። የመልዕክት ልውውጡ ኦፊሴላዊ መግለጫዎችን ማለትም የህዝብ ቆጠራ፣ የወንጀል ትምህርት ቤት፣ ልደት ወዘተ ሁሉ ሊያጠቃልል ይችላል በማለት ያብራራሉ። Koul (1993) አያይዘውም ከአጠቃላይ ጉዳዮች አልፌን ወደ ትምህርታዊ ምርምር ስንመጣ፤የመርሀ ትምህርት ትንተና፣ የማስተማሪያ መፃህፍት የይዘት ቅንብርና ገፅታ ትንተና፣ የትምህርት እቅድ፣ የተለያዩ ትምህርት ቤቶች፣ ተቋማትና ኮሌጆች አቋምና የወደፊት እቅድ ሁሉ በዚህ ተመርምሮ ግንዛቤ ሊገኝበት ይችላል፤ በማለት ያብራሩታል። እንግዲህ ከላይ እንዳየነው ይህ ጥናትም ዋና ትኩረቱ መማርያ መፅሀፍን መገምገም ስለሆነ፣ በይዘት ትንተና ስልት በመማሪያ መፅሀፍ የተካተቱ የቃላት ትምህርቶች ተመርምረዋል። በዚህም በመማሪያ መፃህፍ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶች እንዴት እንደተመረጡ፤ የቃላት ትምህርቶቹ በመፅሀፉ ውስጥ እንዴት እንደቀረቡ እና ሌሎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ትንተናው ተካሂዷል።.

ስለዚህ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት አቀራረብን በተመለከተ የተገኘውን መረጃ ከንድፈ ሀሳብ ክለሳ ጋር በማቀናጀት ለጥናታዊ ጽሁፍ ግብዓት ለመስጠት ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ ሠነድ ፍተሻ በዋንነት ተመርጧል።

### 3.2.2. ቃለመጠየቅ

በዚህ ጥናት ሁለተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት ተደርጎ የተወሰደው ቃለመጠይቅ ነው። ቃለመጠይቅ በቃል የሚቀርብ የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። ይህም ጠያቂው ወይም ተመራማሪው ጥያቄዎቹን ለመላሹ ያቀርባል፤ ያብራራል፣ መላሹ ጋር ፊት ለፊት ሆኖ የተቻለውን ያህል መረጃ ለማግኘት ጥረት ያደርጋል። መላሹ ደግሞ ለተጠየቀው ነገር መልሱን በቃል የሚሰጥበት ዘዴ ነው። ቃለመጠይቅ ርቱእ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጠቀሜታው የጎላ ነው። ቃለ መጠይቅ ከጽሁፍ መጠይቅ በተሻለ መልኩ ለመላሹ ጥያቄዎችን ለማብራራት፣ ግልጽ ያልሆኑ ምላሾችን ይበልጥ ግልጽ እንዲሆኑ ለማድረግ፣ መላሹ ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይሄድና የተፈለገውን መረጃ እንዲሰጥ ለማድረግ ስለሚያስችል ጠንካራ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው። ከመላሾቹ የቃል መልሶች በተጨማሪ ቃል አልባ (non-verbal) ምላሾችን ስለሚያስገኝ ጥሩ አጋዥ መረጃ ይሰበሰባል። በተጨማሪም ቃለመጠይቅ ከጥቂት ባለሙያዎች ብዙ መረጃዎችን በስፋትና በጥልቀት ያስገኛል በማለት ያስረዳሉ። ለመምህራኑ ቃለመጠይቅ ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያት የካበተ የማስተማር ልምድ ስላላቸው፤ በተጨማሪም እነሱ የሰጡት መልስ የጥናታዊ ጽሁፉን መረጃዎች ይበልጥ ተኣማኒ ያደርጋል ተብሎ በአጥኚዋ ስለታመነበት ነው።

ስለዚህም ለተተኳሪዎቹ መምህራን በሙሉ ተመሳሳይ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ ከመማሪያ መፅሐፍ ለተገኘው መረጃ እንደ ማመሳከሪያ ሆነው በትንተናው ተካትቶው ቀርበዋል፡፡

## 3.4 የመረጃ ትንተና

ከመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ይዘት ትንተና እና ከመምህራን ቃልመጠይቅ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ፣ ቀጣዩ ደረጃ የመረጃዎቹ ትንተና ነው፡፡

### 3.4.1 ከሰነድ ፍተሻ የተገኘ መረጃ አተናተን

እንደ Krippendorf (2004፤18) አገዳለጽ የይዘት ትንተና ከታተሙም ሆነ ካልታተሙ ሰነዶች የተገኙ መረጃዎች ምን እንደሆኑ፤ ለምን አገልግሎት እንደዋሉ የሚገመግም፤ ተገቢ መልእክትን አደራጅቶ ወደ አንባቢ ለማስተላለፍ የሚያግዝ ነው፡፡ በተጨማሪም Aweke (2016፤22) እንደሚያስረዱት የይዘት ትንተና በዓይነታዊ ምርምር ውስጥ መረጃዎች መልእክት በሚያስገኙ መልኩ እየተፈተሹና እየተተረጎሙ በተግባር የተደገፈ ዕውቀት እንዲሰጡ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ከመማሪያ መፅሀፉ የተገኙ መረጃዎች ወይም የቃላት ይዘቶች አቀራረብ በየምዕራፉ አንድ በአንድ ከተዘረዘሩ በኃላ በክለሳ ድርሳናት የተጠቀሱት የቃላት ማቅረቢያ ዘዴዎች በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ እንደተደረጉ በዝርዝር በመፈተሽ፤ በአጋዥነት ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በመጨመር እንደ ተመሳስሏቸው ተደራጅተው በሠንጠረዥና በገለፃ በመተንተን ውጤታቸው ቀርቧል፡፡

### 3.5.2 የቃለመጠይቅ አተናተን

የተዘጋጀው ቃለመጠየቅ ከጥናቱ አላማ ሲሆን፤አይነቱም አጠቃላይ ሆኖ ብዛቱ ደግሞ ስድስት ነው፡፡ ስለሆነም በተዛማጅ ጽሁፍ ውስጥ ከተቃኙ የውጪም ሆነ የሀገር ውስጥ ሥራዎች በመነሳት ከአማርኛ መምህራኑ ምላሾች የተገኙት መረጃዎች ከተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በዓይነት እንደተመሳስሏቸው ተደራጅተው በሠንጠረዥና በገለጻ ተቀምጠዋል፡፡

# ምዕራፍ አራት፡ የመረጃ ትንተና

የዚህ ጥናት አላማ በስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ መገምገም ነው፡፡ ስለሆነም በቃለ መጠየቅ ከመምህራን ከተሰበሰቡ መረጃዎች እና መረጃዎቹ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ ከተደራጀ በኋላ በገለጻ ስልት ይቀርባሉ፡፡በመሆኑም የተሰበሰቡት መረጃዎች እየተጠቃለሉ ወይም እየተጨመቁ እንደሚከተለው ተተንትነዋል፡፡

## 4.1. የተተኳሪው መማሪያ መፅሀፍ ዳራ

የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ማጎልበት እንዲሁም የስነ-ጽሁፍና የስነ-ልሳን እውቀትን ማደበር ናቸው፡፡ እነዚህ አጠቃላይ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ከሚያስፈልጉ የትምህርት መሳሪያዎች መካከል ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የመማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ መማሪያ መጽሀፍ ማለት የቋንቋ ተማሪዎች የስነ ልሳንና የተግባቦት ችሎታቸውን እንድያሻሽሉ ታስቦ ተቀርጾ የሚታተም መሆኑን Sheldon, L. (1988፣3) ይገልጻሉ፡፡

በትግራይ ክልል አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች የቀረበው መማሪያ መጽሀፍ፣ የህትመት ዓመት ያልተገለፀበት ሲሆን በስራ ላይ የዋለው በ2015 ዓ.ም ነው፡፡ ይህ መጽሀፍ ምንም አንኳ የህትመት ዓመቱ ባይገለፅም ቀድሞ ስራ ላይ ከነበሩት መማሪያ መጽሀፍት ተሻሽሎ የቀረበ አዲስ መጽሀፍ ነው፡፡ የመጽሀፉ የውጭ ሽፋን ሰማያዊ ቀለም ያለው ሲሆን የውጭ ሽፌኑ የፊት ገፅ የፌደራል መንግስትና የክልሉ መንግስት ትምህርት ቢሮ አርማ የያዘ ነው፡፡ የኋላ ሽፌኑ ላይ ደግሞ የትምህርት ሚኒስቴር አርማ፣ የመጽሀፉን መለያ ቁጥር (ISBN: 978-99944-2646-1) እና የመጽሀፉ ዋጋ (25 ብር) ይዘዋል፡፡

የፊት ሽፌኑ መሀል ላይ የመስማት፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ተግባራትን የሚገልጹ ስዕላዊ መግለጫዎች ሰፍረዋል፡፡ መጽሀፉ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር አስተባባሪነት prin International አዘጋጅነት በ Burda druck india private limited አታሚነት የቀረበ ነው፡፡ መማሪያ መፃፉን አንድ ባንድ ለማየት ያህል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አስር ምዕራፎች፣ ሰባ ሰባት ክፍሎች እና አንድ መቶ ሀያ አራት ገጾች አለው፡፡በተጨማሪም መማሪያ መፅሀፉ ከበስተጀርባው የራሱ ዋቢ መፃህፍት አለው፡፡

## 4.2 በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች መረጃ

በቋንቋ እውቀት ውስጥ የቃላት ሚና የላቀ እንደሆነና የአንድን ቋንቋ ቃላት ባንድ ጊዜና ቦታ ሁሉንም አቅርቦ ማስጠናት እንደማይቻልና ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን መምረጥ አስፈላጊ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ሂደት ውስጥ የትኞቹ ቃላት ለተማሪዎች በመሰረታዊነት እንደሚያስፈልጉ መወሰን ዋና ጉዳይ ነው በማለት Hutchinson and Torres (1994) ይገልጻሉ፡፡ ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን ከአስፈላጊነታቸው በመነሳት መምረጥ እንዳለብንና ልንከተላቸው የሚገቡ መስፈርቶች እንዳሉ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ተተኳሪ መጽሀፍ ከነዚህ የቃላት መምረጫ መስፈርቶች አንጻር እንዴት እንደተዘጋጁ ከሰነድ ፍተሻ እና ቃለመጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በማጠናቀር ተተንትኖ ይቀርባሉ፡፡ የመጽሀፉ አጠቃላይ ይዘት የመጽሀፉ የፊት ሽፋን የውስጥ ገጽ ላይ ተዘርዝረው ቀርበዋል፡፡ በማውጫው እንደሚታየው መጽሀፉ በአስር ምዕራፍችና ሰባ ሰባት ክፍሎች የትምህርት ይዘቶች የተከፋፈሉ የተለያዩ የቋንቋ ይዘቶችን አካቶ ይዟል፡፡ በመጽሀፉ የተካተቱት አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንደሚከተለው በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡

**ሰንጠረዥ1. የተተኳሪ መጽሀፍ አጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች**

| ምዕራፍ | ርዕስ | የትምህርት ይዘት |
|---|---|---|
| አንድ | ቋንቋና የቋንቋ ጥቅም | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ሁለት | መከባበር | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ሶስት | አች ኤይቪ ኤድስ | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| አራት | ወጣትነት | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| አምስት | ሴቶችን ማብቃት | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ስድስት | ታዋቂዋ ሴት | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ሰባት | ተላላፊ በሽታዎች | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ስምንት | የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |
| ዘጠኝ | ባህል | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |

| | | |
|---|---|---|
| አስር | ውሳኔ አሰጣጥ | ማዳመጥ፣ንባብ፣ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው |

በሰንረዥ 4.1 ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው በተተኳሪ መጽሀፍ ውስጥ በእያንዳንዱ ምዕራፍ የተካተቱ ትምህርት ይዘቶች በማዳመጥ፣ ንባብ፣ ቃላት፣ ጽህፈት፣ ሰዋስው ላይ ያተኮሩ ናቸው። ይዘቶቹ የተደራጁት ቋንቋን በመላመድ ሂደት ቀድመው የሚመጡ ክሂሎችን በማስቀደም በትምህርት የምናዳብራቸውን ክሂሎች በማስከተል ነው። በዚህም መሰረት በክፍል አንድ ማዳመጥ፤ በክፍል ሁለት ንባብ፤ በክፍል ሶስት ቃላት፤ በክፍል አራት ጽህፈት እንዲሁም በክፍል አምስት ሰዋስው የሚሉ የትምህርት ይዘቶች ቀርበዋል።

### 4.2.1 ከሰነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ከቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሰነድ ፍተሻና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ከንድፈ ሀሳብ ክለሳው አንጻር እየታየ በሠንጠረዥና በገለጻ ተተንትኖ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 4.2.1. 1. የቃላት ትምህርትን አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ለትምህርት የሚቀርቡ ቃላት በተማሪዎች አዕምሮ የግንዛቤ አሻራ ሊተው በሚችለበት አኳኋን መቅረብ አለባቸው። እንዲሁም ተማሪዎች ዕድሜያቸውን፣ የትምህርት ደራቸውን፣ የትምህርት ዓላማ፣ ለትምህርት የቀረቡትን የአዳዲስ ቃላት ባህርይ ባገናዘቡና ቃላቱን ለመጠቀም በሚያስችል ስልቶች በዳበሩ የቋንቋ መልመጃዎች ውስጥ ማለፍ ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም ከንድፈ ሀሳብ ክለሳ መረዳት እንደሚቻለው በሁለም ደረጃዎች የሚዘጋጁት የቃላት ትምህርት መልመጃዎች የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት የሚያነሳሱ፣ ተሳትፏቸውን የሚያጎለብቱ፣ በራሳቸው ጥረት ቃላቱን እንዲያውቁ የሚገፏፏቸው ሆነው መሰናዳት እንዳለባቸው ነው። በተጨማሪም Morgan and Rinvolucri (1986፣3) እንዳስቀመጡት የቃላት ትምህርት አቀራረብ የተነጣጠለ ሳይሆን አንዱ ክንውን ቀጥሎ ካለው ጋር የተቆራኘና ደረጃ በደረጃ የተዋቀረ ሊሆን ይገባል። ከዚህ በመነሳት አጥኚዋ ከሠነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ ባገኘችው መረጃ መሠረት በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ምሁራን በጠቀሷቸው የቃላት ትምህርት አቀራረብ ስልቶች አኳያ መቅረብ አለመቅረባቸው እንደሚከተለው ተንትኗል።

### 4.2.1.1.1. የቃላት ትምህርቱን አውዷዊ አቀራረብ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ለቃላት ትምህርት አቀራረብ አውድ ትልቅ ድርሻ እንዳለው እና ለቋንቋ ተማሪዎች ተገቢ የሚሆነው የማስተማሪያ ዘዴም ተማሪዎች ለትምህርት ለቀረበው ቋንቋ የሚጋለጡበትን አውድ ማመቻቸትና የአዳዲስ ቃላትን ፍች ከአውዳቸው መገመት እንዲችሉ መገፋፋት መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በመጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡ ምንባቦች ውጭም ቃላትን በአውድ ማቅረብ ተገቢ መሆኑን Lowson and Hogben (1996፣106) ያስረዳሉ፡፡ የቃላት መልመጃዎች በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ሲካተቱ ቃላቱ ከአውድ ጋር ተጣምረው የሚቀርቡና እና ተማሪዎችን ለአውድ በሚያጋልጡ መንገድ ቢቀርቡ ተገቢና የተሻለ መንገድ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ አጥኚዋ ባደረገችው የሠነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ያሉት የቃላት ይዘቶች አብዛኞቹ አውድን መሠረት አድርገው የቀረቡ መሆናቸውን የመፅሀፉ ምዕራፎች ማሳያዎች ናቸው፡፡ የአቀራረብ ስልታቸውም ቃላቱ በምንባብ ውስጥ ከተሰለፉበት ቦታ አንጻር ፍች እንዲሰጡ ማድረግን የሚጠይቁ ናቸው፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አውድን መሠረት ያደረገ የቃላት አቀራረብ በተመለከተ ሁኔታዊ አውድ እና ስነልሳናዊ አውድ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ ሁኔታዊ አውድ ፍች ሲባል በቀረቡ ምንባቦች ውስጥ ቃላት ያላቸውን ፍች እንዲገነዘቡ ማድረግ ሲሆን ከዚህ በመነሳት ተማሪዎች ብዙም ሳይቸገሩ የቃላቱን ፍች ከአገባብ አንጻር ማወቅ እንዲችሉ እገዛ ያደርግላቸዋል፡፡ በሌላ በኩልም ቃላቱ ከምንባቡ ውጪ ራሳቸውን ችለው ሲቆሙ ሌላ ፍች እንዳላቸው እንዲረዱ ያደርጋል፡፡

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ አውድን በስነ ልሳናዊ አቀራረብ እንዲለዩ ቀርቧል፡፡ ስነልሳናዊ አውድ ተማሪዎች በቀረበላቸው ንግግር አማካኝነት የተናጋሪውን ንግግር በማዳመጥ ተናጋሪው በሚያቀርባቸው ቃላት አማካኝነት የተናጋሪውን ማንነት እንዲገልጹ ወይም ዘዬውን እንዲለዩ ያግዛል፤ ይህም ተማሪዎች የቃላትን ስነ ልነሳናዊ ባህሪ እንዲያውቁ የደርጋል፡፡ በዚህ መልመጃ ተማሪዎቹ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪነታቸው ለቃላት ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያግዛቸዋል፡፡

ከዚህ አንጻር በተተኳሪ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፡፡

**ሰንጠረዥ 2. በመማሪያ መጽሀፉ የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብ**

| ተ.ቁ | የቃላት ትምህት አውዳዊ አቀራረብ ሁኔታ | የቀረበ መልመጃ | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በምንባብ ውስጥ ባላቸው አገባብ አንጻር | 4 | 23.53% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 2 | በዐረፍተ ነገር ውስጥ ባላቸው አግባብ | 5 | 29.41% |
| 3 | በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሠርቶ ከማሳየት አንፃር | 8 | 47.06% |
| ድምር | | 17 | 100% |

በሰንረዥ4.2. የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በተተኳሪ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘት አውዳዊ አቀራረብን ነው፡፡ በዚህም መሰረት 23.53% ያህል በምንባብ ውስጥ ባላቸው አገባብ አንጻር፣ 29.41% ያህል በአረፍተ ነገር ውስጥ ባላቸው አግባብና በአረፍተ ነገር ውስጥ ሠርቶ ከማሳየት 47.06% መልመጃዎች ቀርበዋል፡፡ በአጠቃላይ ከቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ውስጥ 23.53% የሚሆኑት አውዳዊ አቀራረብን መሰረት አድርገው የቀረቡ ናቸው፡፡ ይህም የሚያሳየን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አውዳዊ አቀራረብን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ መሆኑን ነው፡፡

እነዚህ ተግባራት በመፅሀፉ በአብዛኛው ምዕራፎች የሚገኙ ሲሆን መልመጃዎቹ ተማሪዎቹ ቃላቱን በምንባቡ ውስጥ ከገቡበት ፍች አንጻር ፍችዎቻቸውን እንዲገምቱ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ይህም ተማሪዎች ብዙም ሳይቸገሩ የቃላቱን ፍች ከአገባብ ማወቅ እንዳለባቸው ትልቅ እገዛ ያደርግላቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት አውድን መሠረት አድርገው መቅረባቸው ተማሪዎች የቃላት ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ትምህርቱ ቶሎ ስለሚገባቸው በአዕምሯቸው ውስጥ ሰርፆ እንዲቀር ከማድረግ አንፃር ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ከዚህ በመቀጠል የቃላት ትምህርት አውዳዊ አቀራረብን በተመለከተ ከመማሪያ መጽሀፉ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመለከታለን፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ መልመጃዎች፡-

ምሳሌ፡- መከባበር ከሚለው ምንባብና ከላይ ከቀረቡት ደብዳቤዎች ውስጥ የአክብሮት ቃላትን ለይታችሁ አውጡ፡፡

1. <u>እርስዎ</u> መልካም ስነ ምግባር <u>አሳይቷል</u>፡፡
2. <u>እርሳቸው</u> ነገ ወደ ሌላ ሀገር <u>ይሄዳሉ</u>፡፡
3. <u>እባክዎ</u> ተራዎን ጠብቀው <u>ይስተናገዱ</u>፡፡

ምሳሌ 2፡-

1. የሚከተሉት ሀሳቦች ከምንባቡ የተውጣጡ ናቸው፡፡ እነዚህን መነሻ ሀሳቦች በመጠቀም አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ ቀውስ ያስከትላል፡፡

ምሳሌ 3፡- የሚከተሉትን ቃላት በመጠቀም ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. መዘናጋት
2. ሳል
3. ተላላፊ
4. ክትባት
5. ጥናቃቄ

መምህራኑ የሰጡት መልስ እና በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት አውድ መሠረት አድርገው መቅረባቸው ተመሳሳይነትና ተያያዥነት አላቸው፡፡ ይህም የሚያሳየው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት በጥሩ ሁኔታ መቅረባቸውን ነው፡፡ በአጠቃላይ ከመምህራኑ እና ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መልስ መሰረት በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡት ቃላትን በአውድ መሠረት አድርገው መቅረባቸው ተማሪዎች የቃላት ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ትምህርቱ ቶሎ ስለሚገባቸው በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ቃላቱ በአዕምሯቸው ውስጥ ሰርፆ እንዲቀር ከማድረግ አንፃር ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አውዳዊ አቀራረብን መሰረት አድርገው የተዘጋጁ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.2.1.1.2. የቃላትን የፍች ዝምድና አቀራረብ የተመለከተ መረጃዎች ትንተና

ተማሪዎች የቃላትን ንበት መመሳሰል መሰረት አድርገው ቃላት ቢያከማቹም በትምህርት እየገፉ ሲሄዱ ቃላትን በአዕምሮ ስሌዳቸው ቀርፀው የሚያስቀምጡት በፍቺያቸው አማካኝነት ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በመካከለኛና በከፍተኛ ደረጃ ላይ እያሉ ቃላትን በዝምድናቸው መነሻነት ማቅረብ በቀላሉ የቃላትን ፍች እንዲገነዘቡ ያደርጋል በማለት McCarthy (1990፣39) ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም ለተማሪዎች አስፈላጊ የሆነውን የቃላት እውቀት ለማስጨበጥ የአዳዲስ ቃላት ፅንሰ ሀሳባዊና አገልግሎታዊ ልዩነቶችን በሚያሳይ መንገድ ማቅረብ ይገባል፡፡ በመሆኑም ቃላትን በተመሳስሏቸውና በተቃርኗቸው፣ የከታች ተከታች ግንኙነት እንዲሁም በአብሮ ተሰላፊነታቸው ለይቶ ማቅረብ ተገቢ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በተተኳሪ መማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘት መልመጃዎች ከቃላት የፍች ዝምድናዎች አኳያ እንዴት እንደቀረቡ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

**ሠንጠረዥ 3. የቃላት ትምህርት የፍች ዝምድና አቀራረብ**

| ተ.ቀ | የቃላት የፍች ዝምድና አይነት | የተግባራት ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በፍች ተመሳስሎና ተቃርኖ የቀረቡ | 16 | 80% |
| 2 | በማጠቃለልና በመዘርዘር ሁኔታ የቀረቡ | 0 | 0 |
| 3 | በአብሮ ተሰላፊነት የቀረቡ | 4 | 20% |
| | ድምር | 20 | 100% |

በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው በፍች ተመሳስሎና ተቃርኖ 80% ተግባራት የቀረቡ ሲሆን በቃላት አብሮ ተሰላፊነት የቀረቡ 20% ተግባራት በበኩላቸው ዝቅተኛውን ድርሻ ይዘዋል፡፡ የቃላት አብሮ ተሰላፊነት ቃልን ፍች ጋር ለመረዳትና ሰፊ ፍችን ለማስተማር እንዲሁም በትውስታ ማህደር ለማከማቸትና የፍች አካባቢን ለመረዳት ጥቅሙ የጎላ ነው፡፡ በሌላ በኩል በማጠቃለልና መዘርዘር የቀረቡ ተግባራት በመጽሀፉ ውስጥ አልተገለፁም፡፡

በመሆኑም መጽሀፉ የቃላት አብሮ ተሰላፊነትን በዝቅተኛ ደረጃ እንዲሁም ማጠቃለልና መዘርዘርን ከነጭራሹ አለማካተቱ ትልቅ ክፍተት አለው፡፡ በአጠቃላይ የፍች ዝምድናን መሰረት አድርገው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ችግር ያለበት መሆኑን ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡ ከዚህ በመቀጠል የቃላት ትምህርት የፍች ዝምድና አቀራረብን በተመለከተ ከመማሪያ መጽሀፉ ምሳሌዎችን እንመለከታለን፡፡

ምሳሌ፡- 1 በተመሳሳይ እና በተቃራኒ የቀረቡ መልመጃዎች

በ “ሀ” ክፍል ለተጻፉት ቃላት ተቃራኒያቸውን ከ “ለ“ክፍል ጋር አዛምዱ (ገጽ 74)

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ጎበዝ | ሀ. መጨረሻ |
| 2. ዘመድ | ለ. ማፊሪያ |
| 3. መጀመሪያ | ሐ. ቅርበት |
| 4. መኩሪያ | መ. ትዳር |
| 5. ፍቅር | ሠ. እቅጩን ተናገር |

6. ገመተ　　　　　　　ረ. ባእድ

7. ገባ　　　　　　　ሰ. ወጣች

8. ርቀት　　　　　　　ሸ. ጥላቻ

በ “ሀ” ክፍል ለተጻፉት ቃላት ተመሳሳያቸውን ከ “ለ“ ክፍል ጋር አዛምዱ (ገጽ 110)

| ሀ | | ለ |
|---|---|---|
| 1. | እንግዳ | ሀ. በጣም አስደሳች |
| 2. | ሰርግ | ለ. የጋብቻ ስነ ስርዓት |
| 3. | ማራኪ | ሐ. ወደኋላ የሚያስቀር |
| 4. | ጎታች | መ. የሐዘን ስርዓት |
| 5. | ለቅሶ | ሠ. አጌጠ |
| 6. | ተዋበ | ረ. ገባር |
| | | ሰ. ድግስ |
| | | ሸ. ባህል |

በአብሮ ተሰላፊነት ለናሙና የቀረቡ ተግባራት፡-

ምሳሌ፡- 1

1. የሚከተሉት ሀሳቦች ከምንባቡ የተውጣጡ ናቸው፡፡ እነዚህን መነሻ ሀሳቦች በመጠቀም አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

   ሀ. ከፍተኛ ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ (ገጽ 41)

   ለ. መዘናጋት

   ሐ. ሳል

   መ. መድሀኒት

   ሠ. ምርመራ

በአጠቃላይ ከቃለመጠይቅና ከሰነድ ፍተሻ ከተገኘው መረጃ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሞላ ጎደል የቃላቱን የፍች ዝምድና መሰረት አድርገው የቀረቡ

እንደሆኑ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል። ይሁን እንጂ የቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ ከነጭራሹ በአንድም ቦታ አለመቅረቡ ከዚህ አንጻር ክፍተት ያለበት መሆኑን መረዳት ይቻላል።

### 4.2.1.1.3. ቃላትን በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ

በክለሳ ድርሳኑ ምሁራኑ እንደገለፁት በመዝገበ ቃላት ተደግፎ የሚቀርብ የቃላት ትምህርት አቀራረብ በአጠቃቀም ብልሃት ላይ ትኩረት አድርጎ ከቀረበ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ባስፈለጋቸው ጊዜ ስለቃላት የሚፈልጉትን መረጃ ለማግኘት መዝገበ ቃላትን የመጠቀም ልምድ እንዲያዳብሩ ከማድረግ አንፃር ድርሻው የጎላ ነው። በመሆኑም በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ተደግፈው የሚቀርቡ የቃላት ትምህርት ተግባር ስለ አጠቃቀም አንዳንድ መመሪያ በመስጠት ጭምር ሊቀርብ ይገባል።

በመሆኑም የቃላት ትምህርትን መዝገበ ቃላትን ተደግፈው የቀረቡት የቃላት ትምህርቱን የተቃና ያደርገዋል። ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ ትምህርቶችን ከዚህ በታች በተቀመጠው ሠንጠረዥ እንመልከት።

**ሠንጠረዥ4. መዝገበ ቃላትን ተደግፈው የቀረቡት ቃላት**

| ተ.ቁ | የመመሪያዎች አቀራረብ ሁኔታ | የተግባር ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በአዛምድ መልክ | 1 | 6.25% |
| 2 | ቀጥታ በመዝገበ ቃላት በመታገዝ ፍቻቸውን እንዲፈልጉ | 15 | 93.75% |
| ድምር | | 16 | 100% |

በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው በአዛምድ መልክ 6.25% ተግባራት የቀረቡ ሲሆን ቀጥታ በመዝገበ ቃላት በመታገዝ ፍቻቸውን እንዲፈልጉ የቀረቡ ደግሞ 93.75% ተግባራት ሲሆኑ በጣም ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል።

በመዝገበ ቃላት ተደግፈው ለናሙና የቀረቡ ተግባራት፡-

1. በምንባቡ ውስጥ ከዚህ በፊት የማታውቋቸውን ቃላት ካሉ ለይታችሁ አውጡ። ከዚያም የእነዚህን አዳዲስ ቃላት ትርጉም በመዝገበ ቃላት በመታገዝ ፈልጉ።
2. የሚከተሉትን ቃላት እማሬዊና ፍካሬዊ ፍች ጻፉ (ገጽ 89)

ምሳሌ፡-

| | እማሬዊ | ፍካሬዊ |
|---|---|---|
| ወቃ | እህል አበራየ | በጣም ደበደበ |
| ቀለለ | ክብደት አጣ | ተዋረደ |
| ተተከሰ | ጥይትጮሀ | በፍጥነት አደገ |

አጥኚዋ ከመምህራኑ ከሰጡት መልስ መገንዘብ እንደቻለችው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ተደግፈው የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች ውስን መሆናቸውን ነው፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ የቃላት ትምህርት ይዘት መልመጃዎች በመዝገበ ቃላትን ተደግፈው  የቀረቡ ቢሆኑም ከአውድና ከአውድ ውጪ የቀረቡ ናቸው፡፡ በተለይ ከምንባብ በሚወጡት ቃላት ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ ተማሪዎች ከምንባብ በሚወጡት ቃላት ላይ ትኩረት አድርገው ከውጭ በርካታ ቃላትን ማወቁ ላይ ውስንነት እንዲታይባቸው ያደርጋል፡፡ ሌላው የቃላት ፍችን በተመለከተ ተማሪዎች መዝገበ ቃላትን ገልጠው ለቃላት ፍች እንዲሰጡ የሚያደርግ መልመጃ ውስን በመሆኑ ተማሪዎች ቤተ-መጻሕፍትን እንዲጠቀሙ አያበረታታቸውም፡፡ ስለሆነም ከመጽሀፉና ከመምህራኑ የተገኙት መረጃዎች የተጣጣሙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በመሆኑም ቃላትን በመዝገበ ቃል አስደግፎ ከማቅረብ አንጻር ክፍተት ያለበት መሆኑን የጥናቱ ውጤት ያሳያል፡፡ ይህም በተማሪዎቹ የቃላት እውቀት ላይ የራሱ የሆነ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች በቂ የመዝገበ ቃላዊ ፍች ትምህርት ካላገኙ ቋንቋው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስላልሆነ የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች የማወቅ ውስንነት ይኖርባቸዋል፡፡ ስለዚህ ተማሪዎቹ ቋንቋ እንዲያውቁ በመማርያ መጽሀፉ ውስጥ በመዝገበ ቃላት ትምህርት በአብዛኛው ቦታ መቅረብ ነበረባቸው፡፡

በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሀፉ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ መሆናቸው በድክመት የሚታይ ነው፡፡

### 4.2.1.1.4 ቃላትን ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብ

የቃለት ትምህርት መልመጃዎች ለተማሪዎች ሲቀርቡ ለመለማመድ እንዲያግዛቸው ግልፅ ሆኖ በተብራራ ሁኔታ የሰፈረ መመሪያ ሊኖረው እንደሚገባ በክለሳ ድርሳኑ ተገልጿል፡፡ ይህም የሚያመለክተን የቃላት ትምህርት ተግባራትና መልመጃዎች የቀረቡበት ዓላማ ከግብ የሚያርሰው መመሪያዎቹ ለተማሪዎች ግልፅ ሆነው ሲቀርቡ መሆኑን ነው፡፡ ተማሪዎች የቀረቡላቸው መልመጃዎች ገብቷቸው ሊለማመዱ የሚችሉት በመጽሀፉ የሚቀርቡ ተግባራት በግልጽ

መመሪያዎችና ምሳሌዎች ተደግፈው ሲቀርቡ ነው፡፡ ይህንንም መሰረት በማድረግ በተተኳሪ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ተግባራት በግልጽ መመሪያዎች የተደገፉ መሆን አለመሆናቸውን በሰነድ ፍተሻ ታይቷል፡፡

**ሠንጠረዥ 5. የቃላት ትምህርት ተግባራት የመመሪያዎች አቀራረብ**

| ተ.ቁ | የመመሪያዎች አቀራረብ ሁኔታ | የተግባር ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | በምሳሌ የተደገፈ | 17 | 53.13% |
| 2 | በምሳሌ ያልተደገፈ | 15 | 46.87% |
| ድምር | | 32 | 100% |

በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ እንደምንረዳው በምሳሌ የተደገፈ 53.13% ተግባራት የቀረቡ ሲሆን በምሳሌ ያልተደገፈ የቀረቡ ደግሞ 46.87% ተግባራት ድርሻ ይዘዋል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ በምሳሌ ተደግፈው ከቀረቡ መልጃዎች (ገጽ 41)

**ምሳሌ፡-**

1. መዘናጋት

በኤች አይ ቪ ኤድስ ጉዳይ መጠንቀቅ እንጂ ለአፍታም ቢሆን መዘናጋት የለብንም፡፡

2. ሳል

በኤች አይ ቪ ኤድስ ቫይረስ የተያዘ ሰው ከሚያሳያቸው ምልክቶች መካከል አንዱ ሳል ነው፡፡

ከምንባቡ ያገኛችኋቸውን አዳዲስ ቃላት ለይታችሁ ጻፉና በቃላቱ ዓረፍተ ነገር በመመስረት ተለማመዱ፡፡ (ገጽ 75)

ምሳሌ፡-

- ምዝገባ

ነገ የአዲስ ተማሪዎች ምዛገባ ቀን ነው፡፡

- ስፖርት

ስፖርት የሚለውን የተውሶ ቃል በአማርኛ በብዛት እንጠቀምበታለን፡፡

**ምሳሌ፡- በምሳሌ ያልተደገፉ መልመጃዎች**

በምንባቡ ውስጥ ከዚህ በፊት የማታውቋቸውን ቃላት ካሉ ለይታችሁ አውጡ፡፡ከዚያም የእነዚህን አዳዲስ ቃላት ትርጉም በመዝገበ ቃላት በመታገዝ ፈልጉ፡፡

በአጠቃላይ ከሰነድ ፍተሻና ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ በመምሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራት አብዛኛው ቦታ ላይ በግልጽ መመሪያዎች እንደቀረቡና በምሳሌ አስደግፈው ከማቅረብ አንጻር ግን ክፍተት እንዳለባቸው ያመለክታል፡፡

### 4.2.1.1.5 ቃላትን ከክሂል ትምህርቶች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ

ተማሪዎች ቃላትን በሚገባ እንዲረዳቸውና አይረሴ በሆነ መንገድ እንዲገነዘቧቸው ከክሂል ትምህርቶች ጋር ሊለማመዳቸው ይገባል፡፡ ተማሪዎች ያገኟቸውን አዳዲስ ቃላትን አስታውሰው ትርጉም ባለው አውድ መጠቀም የሚችሉት የመቀበያ ክሂሎችን ተጠቅመው ባገኙት እውቀት ነው፡፡ በመሆኑም የቃላት ትምህርትን ከክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብ ትምህርቱን የተቃና ያደርገዋል፡፡ ከዚህ አንፃር በተተኳሪ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡ ቃላትን ከክሂል ትምህርቶችን በሠንጠረዥ እንመልከት፡፡

**ሠንጠረዥ 6. የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አቀራረብ**

| ተ.ቁ | የተግባራቱ የአቀራረብ ሁኔታ | የተግባር ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ከማዳመጥ ክሂል ጋር የቀረቡ | 3 | 15.79% |
| 2 | ከንባብ ክሂል ጋር የቀረቡ | 4 | 21.05% |
| 3 | ከንግግር ክሂል ጋር የቀረቡ | 4 | 21.05% |
| 4 | ከጽህፈት ክሂል ጋር የቀረቡ | 8 | 42.11% |
| ድምር | | 19 | 100% |

ከላይ የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በተተኳሪ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ከሌሎች የክሂል ትምህርት ይዘቶች ጋር ያላቸውን ቅንጅታዊ አቀራረብ ነው፡፡ በዚህም መሰረት መጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡ ተግባራት ከክሂል ትምህርት ጋር ማለትም ከማዳመጥ(15.79%)፣ ከንባብ(21.05%)፣ ከመናገር(21.05%) እና ከመጻፍ ክሂል (42.11%) ጋር ተቀናጅተው የቀረቡ

ናቸው። በተለይም ለጽህፈት ክሂሎች የተለየ ትኩረት እንደተሰጠ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ መልመጃዎች ያሳያሉ። ይህም የሚያመለክተው በመጽሀፉ ለክህሎት አቀራረብ የተሻለ ትኩረት የተሰጠ መሆኑን ነው።

የቃላት ትምህርት ከክሂሎች ጋር ያላቸው ቅንጅታዊ አቀራረብ በተመለከተ በመማሪያ መጽሐፉ የቀረቡ መልመጃዎች

**ምሳሌ፡-1**

1. የመጻፍ ችሎታን ማዳበር (ገጽ 55)

   ከተወሰኑ ቃላት ብዙ ዓለፍተ ነገሮች መስራት እንደሚቻል ከመምህራችሁ ተረዱ። በመቀጠልም በሳጥኑ ውስጥ ያሉትን ቃላት በመጠቀም ልዩ ልዩ ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

2. ከታች የቀረበውን ምንባብ ከማንበባችሁ በፊት እነዚህን ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች መልሱ (ገጽ 20)
3. የተነበበላችሁን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ። (ገጽ 15)

በአጠቃላይ መምህራኑ የሰጡት ቃለ መጠይቅ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘት መልመጃዎች ራሳቸውን ችለው ከመቅረባቸው ባሻገር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅተው በተለያዩ ቦታዎች ላይ በመልመጃዎች የቀረቡ መሆናቸውን አብራርተዋል። በመሆኑ መምህራኑ ከሰጡት መልስ የምንረዳው በመመሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘት መረጃዎች ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር በጥሩ ሁኖታ ተቀናጅተው የቀረቡ መሆናቸውን ነው። በተጨማሪም ከመምህራኑና ከሰነድ ፍተሻ የተገኘው መረጃ ጋር የተጣጣመ ነው። በመማሪያ መጽሀፉ ከቀረቡት የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ከቋንቋ ክክሂል ጋር በቅንጅት የቀረቡ መሆናቸውን በሰነድ ፍተሻው ተረጋግጧል።

## 4.2.1.1.6 የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

የቃላት ትምህርት ማቅረቢያ ስልት የጎላ ጠቀሜታ እንዳላቸው የሚታመንባቸው ቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደታቸውን በመከተል ማቅረብ ነው። በቋንቋ ውስጥ በአንጻራዊ አነጋገር ጥቂት ቁጥር ያላቸውን የቃላት አፈጣጠር ሂደቶች በመከተል ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን አዳዲስ ቃላትን መፍጠር ይቻላል። ቃላት የተለያዩ አርቢ ምዕላዶችን በመጨመር ልዩ ልዩ ቅርፆች ሊይዙ ይችላሉ ። ስለዚህ ቃላት የእርባታና የምስረታ ሂደታቸውን ተከትለው ማቅረብ የቀረቡት

ቃላት እንዴት እንደሚረቡ እና እንደሚመሰረቱ ተማሪዎች እንዲያውቁ ለማድረግ ነው። በቃላት እርባታ ጊዜ የቃል ክፍሎች እንዲረቡ ለማድረግ እርባታቸው ከሰዋስው ባህሪያት አኳያ መሆን አለበት። የሰዋስው ባህሪያት የሚባሉት እንደ መደብ፣ ጾታ፣ ቁጥር፣ ሙያ እና ጊዜ ያሉት ናቸው። ቃላት በዚህ ባህሪያት የተለያዩ ቅርፅ ያሳያሉ። ይህ ታዲያ ለተማሪዎች መቅረቡ የበለጠ የቋንቋ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል።

ሌላው የአቀራረብ ስልት ደግሞ የቃላትን የምስረታ ሂደት ተከተሎ ማቅረብ ነው ፣ምስረታውም ከስም፣ ከቅፅል፣ ከግስ ሊሆን ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የቃል ክፍላቸውን ሊቀይሩ ይችላሉ። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ቃላት በዚህ ስልት ቢቀርቡላቸው የቃል ክፍሎችን እየቀየሩ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፤ በማለት የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ።

**ሠንጠረዥ 7. የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት በተመለከተ ያላቸው አቀራረብ**

| ተ.ቁ | የተግባራቱ የአቀራረብ ሁኔታ | የተግባር ብዛት | |
|---|---|---|---|
| | | በቁጥር | በመቶኛ |
| 1 | ከሰዋስው ባህሪያት የቀረቡ | 3 | 42.86% |
| 2 | የምስረታ ሂደት የቀረቡ | 4 | 57.14% |
| ድምር | | 7 | 100% |

ከላይ በሰንጠለዡ የቀረበው መረጃ የሚያሳየው በተተኳሪ መጽሀፍ ውስጥ የተካተቱ የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላትን እርባታና ምስረታ አቀራራብ ከሰዋሰው እና ከምስረታ ጋር ያላቸውን አቀራረብ ያሳያል። በዚህም መሰረት በመጽሀፉ ውስጥ ከቀረቡ ተግባራት ከሰዋሰው (42.86%) እና ከምስረታ ሂደት(57.14%) ናቸው። ይህም የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት የሚያመለክተው በመጽሀፉ መጠናዊ ትኩረት የተሰጠ መሆኑን ነው።

የቃላትን እርባታና ምስረታ የተመለከቱ መልመጃዎች

ምሳሌ1፡- የሚከተሉትን ቃላት በማገናኘት የተለያዩ ዐረፍተነገሮች መስርቱ (ገጽ 55)

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 1. ሄደች | እሷ | ወደ | እና | እሱ |
| 2. በሉ | ረጅም | ይመጣል | ገዙ | በሬ |
| 3. ምሳ | ገበያ | ነው | ናቸው | ናት |

ምሳሌ 2፡- በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ቅጥያዎች በመለየት የእርባታ ወይም የምስረታ ቅጥያዎች መሆናቸውን በምሳሌ እንደተሰጠው በምልክት አሳዩ (ገጽ 87)

**ሠንጠረዥ 8. የቃላትን እርባታና ምስረታ ስርዓት በተመለከተ ያላቸው አቀራረብ**

| ቃላት | የእርባታ | የምስረታ |
|---|---|---|
| ፈለግህ | | |
| ፈለገች | | |
| ይፈልጉ | | |
| ፈላጊ | | |
| ፍለጋ | | |
| ፍላጎት | | |

## 4.2.1.2 የቃላት ትምህርትን ይዘት አመራረጥ የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

በቋንቋ እውቀት ውስጥ የቃላት ሚና የላቀ እንደሆነና የአንድን ቋንቋ ቃላት ባንድ ጊዜና ቦታ ሁሉንም አቅርቦ ማስጠናት እንደማይቻልና ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን መምረጥ አስፈሊጊ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በተጨማሪም በመማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት ሂደት ውስጥ የትኞቹ ቃላት ለተማሪዎች በመሰረታዊነት እንደሚያስፈልጉ መወሰን ዋና ጉዳይ ነው በማለት Hutchinson and Torres (1994) ይገልጻሉ፡፡ ለትምህርትነት የሚቀርቡ ቃላትን ከአስፈላጊነታቸው በመነሳት መምረጥ እንዳለብንና ልንከተላቸው የሚገቡ መስፈርቶች እንዳሉ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ ተተኳሪ መማሪያ መፅሀፉ ከነዚህ የቃላት መምረጫ መስፈርቶች አንጻር እንዴት እንደተዘጋጀ ከሰነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ የተገኙትን መረጃዎች በማጠናቀር አጥኚዋ እንደሚከተለው አቅርባለች፡፡

### 4.2.1.2.1. የተማሪውን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ

ተማሪ እንዲማር የሚቀርቡለት ቃላት ሲመረጡ ሊስተዋሉ ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ የተማሪዎች ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ አንድ ነው፡፡ McCarthy (1990፣69) እንደሚያስረዱት የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ የተማሪውን ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃና የቀድሞውን እውቀት ያገናዘበ መሆን እንደለበት ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም Atkins and Etal (1996፣33)

እንደሚገልፁት የመማሪያ መጽሀፍ አዘጋጆች ቃላትን ለመምረጥ ሲነሱ በመምህራን የተካሄደ የተማሪዎች ፍላጎት አሰሳዎችን፣ በግል ደረጃ እያንዳንዱ ተማሪ ይኖረዋል ተብሎ የሚታሰበውን ፍላጎትን በመተንበይ ማካተት እንደሚኖርባቸው ያስረዳሉ፡፡

ምሳሌ1. "ሽውራራው ውሳኔ" በሚለው ግጥም ውስጥ ያሉት ቃላት ከመደበኛው ቃላት የተለዩ ናቸው፡፡ በተጨማሪም በግጥሙ ውስጥ የተመረጡት ቃላት አዲስ እንደመሆናቸው መጠን የቃላቱን ፍች ለማወቅ ሁሉም ተማሪዎች ለሚነበበው ጽሁፍ ትኩረት ይሰጣሉ፤ ምክንያቱም ተማሪዎች በነዚህ ተዘወታሪ ባልሆኑ ቃላት የተጻፉትን ነገሮች ማዳመጥ ወይም ማንበብ ስለሚፈልጉ ነው፡፡ በዚህ የተነሳ አስተማሪው ተማሪዎቹ ለነገሩ ትኩረት መስጠታቸውን ካስተዋለ በኋላ የተለያዩ መልመጃዎችን ሰጥቶ ሊያሰራቸው ይችላል፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ተማሪዎች ከማህበረሰቡ ወግና ሥርዓት ወጣ ያለ ተግባር እንደሚፈጽሙ በመጠቆም የአብዛኛው ተማሪ ፍላጎት ደግሞ ይህ በማህረሰቡ የሚከናወን ያልተገባ ተግባርን ተማሪዎች ለማስተማር የተመረጡ ቃላት በመሆናቸው፣ ተማሪዎችም በነዚህ ግጥም ውስጥ የቀረቡት ቃላት የሚሰጣቸውን መልመጃ ሳይሰለቹ በፍላጎታቸው በንቃት ተሳትፈው ይሠራሉ፡፡ በተጨማሪም አብዛኞቹ ተማሪዎች በዚህ አፍላ ዕድሜያቸው ሳያስተውሉ የሚያደርጓቸውን ድርጊቶችና ውሳኔያውን የሚገልጹ ቃላት ፈጥረው ይጠቀማሉ፡፡

ምሳሌ2. ገጽ 118 ላይ በቀረበው ግጥም ውስጥ ገጸ ባህሪዋ ቸኩላ በመወሰን ያደረሰባትን ጉዳት ያሳያል በዚህም በደሏን ለመግለጽ የተለያዩ ቃላት በግጥም ውስጥ ተጠቅማለች ፡፡ ቃላቱ ተለምዷዊ በመሆናቸው ተማሪዎች ያላቸውን የቃላት እውቀት እንዲያዳብሩ እድል ይሰጣቸዋል፡፡

በተተኳሪ የክፍል ደረጃ ያሉት ተማሪዎች የችኩላነት ባህርይ እንዳለባቸውም እላይ ከተጠቀሰችው ገጸ ባህርይ ማወቅ ይቻላል፡፡ በአጠቃላይ በተተኳሪ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተመረጡት ቃላት አብዛኞቹ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ዕድሜና የትምህርት ደረጃን መሠረት አድርገው እንደተመረጡ ከሠነድ ፍተሻና ቃለ መጠይቅ ማወቅ ተችሏል፡፡

### 4.2.1.2.2. የቃላት የድግግሞሽ መጠን

Nunan (1991፣118) እንደሚያስረዱት የማስተማሪያ መፅሀፍ ሲዘጋጅ የቃላት ትምህርት ይዘታቸውን ለመወሰን የቃላት የድግግሞሽ መጠን እንደ ጠቃሚ መስፈርት ነው፡፡ በተጨማሪም በዕለት ከዕለት ተግባቦት ሂደት የሚያገለግሉ ተዘውታሪ ቃላትን ለይቶ ማስተማር ተማሪዎችን በቋንቋ ለመጠቀም የሚያስችል ውጤታማ የማስተማር ስልት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ጋር

በተያያዘ McCarthy (1990፣66) በማንኛውም ቋንቋ አጠቃቀም እጅግ በጣም ተደጋግመው የሚከሰቱ ቃላት ለዚያ ቋንቋ ጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ለማሳደግ ተዘውታሪ ቃላትን አስቀድሞ ማስተማር ወሳኝ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

እላይ ከተጠቀሱት የዘርፉ ምሁራን ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚቀርቡ ቃላት ተዘውታሪ ቃላት ሊሆኑ እንደሚገባና የተማሪዎችን የተግባቦት አቅም ለማሳደግ ተዘውታሪ ቃላትን አስቀድሞ ማስተማር ወሳኝ እንደሆነ ነው፡፡ ስለዚህ አጥኚዋ ባደረገችው የሠነድ ፍተሻ እና ቃለመጠይቅ በተተኳሪ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የቀረቡትን የቃላት ይዘት መልመጃዎች የድግግሞሽ መጠን በመፈተሽ የትኞቹ የቃላት ይዘቶች እንደተካተቱ፣ መካተት ከሚገባቸው ቃላዊ ይዘቶች ውስጥ የትኞቹ እንዳልተካተቱ እና ምን ያህል ጊዜ እንደተካተቱ በመፈተሽ እንደሚከተለው ለማቅረብ ጥረት ተድርጓል፡፡

**ሠንጠረዥ 9. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት የቃላት ይዘት የድግግሞሽ መጠን**

| ተ.ቁ. | ይዘቶች | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | ፈሊጣዊ ቃላት | 2 |
| 2 | ባዶ ቦታ በቃላት መሙላት | 1 |
| 3 | ተመሳሳይ ተቃራኒ ቃላት | 2 |
| 4 | እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች | 3 |
| 5 | መዝገበ ቃላዊ ፍች | 3 |
| 6 | የቃላት አውዳዊ ፍች | 8 |
| 7 | የቃላት ምስረታ/እርባታ | 5 |
| 8 | የቃልና የምዕላድ አንድነት | 1 |
| 9 | የቃል ክፍሎች | 9 |
| 10 | ጥምር ቃላት | - |
| 11 | ቃላትን በአገባብ ቅደም ተከተል በማደራጀት አረፍተ ነገር ማስተካከል | - |
| 12 | የቃላት ከታች ተከታች የፍች ግንኙነት | - |
| 13 | የቃላት የፍች ልዩነት | - |
| 14 | አብሮ ተሰላፊ ቃላት | 1 |
| 15 | አያያዥና የመሸጋገሪያ ቃላት | 3 |

በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ጥምር ቃልን፣ የቃላት ከታች ተከታች የፍች ግንኙነትን፣ የቃላትን የፍች ልዩነት፣ ቃላትን በአረፍተነገር ውስጥ በአገባብ ቅደም ተከተል ማደራጀትን የሚወክሉ መልመጃዎች አልተካተቱም። የቃል ምስረታን በሚመለከት አምስት ጊዜ ወይም 14% ጊዜ ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ሲሆን የቃላት አውዳዊ ፍችን በተመለከተ ስምንት ጊዜ ወይም 17.2% ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ነው። በሠንጠረዥ 9 በብዛት ተደጋግሞ የቀረበ ይዘት ቢኖር አውዳዊ የቃላት አቀራረብ ስልት ነው። በአጠቃላይ እላይ ከተገለጸው መረዳት እንደሚቻለው በተተኳሪ መማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ይዘቶች የድግግሞሽ መጠን ያልተመጣጠነ፣ መካተት ሲገባቸው ያልተካተቱ ይዘቶች እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል። እንደዚህ ዓይነት አቀራረብ ደግሞ ተማሪዎች በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱትን የቃላዊ ይዘቶች መልመጃዎችን በተገቢ ሁኔታ ሰርተው እንደይለማመዱ አሉታዊ ተጽእኖ ሊፈጥርባቸው ይችላሉ።

### 4.2.1.2.3. የቃላት የፍች ሽፋን

Lewis (1993) እንደሚገልጹት በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት ፍችን በማስተላለፍ በኩል እኩል የአገልግሎት ሽፋን የላቸውም። አንደንድ ቃላት በርካታ ፍችን መሸከም በመቻላቸው በተለያዩ አውዶች ሰፋ ያለ ፍችን ያስተላልፋሉ።ከዚህ አንጻር Wallace (1988፣18-19) እንደሚገልጹት አንዳንድ ቃላት ሰፊ ፍች ስላላቸው ሀሳብን አምቀው መያዝ ችሎታ ሲኖራቸው አንዳንዶቹ ደግሞ ጠባብ ፍች ስላላቸው ሰፊ ፍች ባላቸው ቃላት ስር ይጠቃለላሉ። በመሆኑም ቃላት ከሚሰጡት ትርጉም አንጻር እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ይኖራቸዋል። በንግግርም ሆነ በፅሁፍ ተግባቦታዊ አውድ ውስጥ ተደጋግመው የሚከሰቱና ሰፊ የፍች ሽፋን ያላቸው ቃላት በቃላት ትምህርት ይዘትነት ተመርጠው ሊካተቱ ይገባል።

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ በቃላት ይዘትነት የተካተቱት ቃላት ተደጋግመው የሚከሰቱና ሰፊ የፍች ሽፋን ያላቸው ናቸው። በተለይ በፍካሬያዊ እና እማሬያዊ ፍች የሚከሰቱትን ቃላት አካቷል። እነዚህ ይዘቶች ተመርጠው መካተታቸው ተማሪዎች የቃልን ሰፊ ፍች ማለትም አንድ ቃል በርካታ ፍች ሊኖረው እንደመቻሉ መጠን የተለያዩ ፍችዎችን የማወቅ ችሎታቸው ይጨምራል።

ምሳሌ 1. "ወቃ" የሚለው ቃል በእማሬያዊ ፍችው እህል አበራየ፣ አሽ ማለት ሲሆን፣ ፍካሬያዊ ፍችው ደግሞ በጣም ደበደበ ማለት እንደሆነ ገጽ 89 ላይ ተቀምጧል።

ምሳሌ 2. "ቀለለ" የሚለው ቃል በአማሬያዊ ፍችው ክብደት አጣ ማለት ሲሆን፣ ፍካሬያዊ ፍችው ደግሞ በፍጥነት አደገ ማለት እንደሆነ ገጽ 89 ላይ ተገልጿል፡፡

ምሳሌ 3. "ተተኮሰ" የሚለው ቃል በአማሬያዊ ፍችው ጥይት ጮሀ ማለት ሲሆን፣ ፍካሬያዊ ፍችው ደግሞ ተዋረደ ማለት እንደሆነ ገጽ 89 ላይ ይገኛል፡፡

ተማሪዎች ከዚህ በመነሳት የአንድ ቃል በርካታ ፍች ማወቅ እንዲችሉ ትልቅ እገዛ ያደርግላቸዋል፡፡ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቃላት የፍች ሽፋንን መሠረት አድርገው የተመረጡ ቃላት መካተታቸው መግለፅ ይቻላል፡፡ ስለዚህ አጥኚዋ ባደረገችው የሰነድ ፍተሻና ቃለመጠይቅ የፍች ሽፋንን መሠረት አድርገው በተተኳሪ መፅሀፍ ውስጥ ቃላትን ከመምረጥ አኳያ መልካም ሥራ እንደተሠራ መገንዘብ ተችሏል፡፡

### 4.2.1.2.4. የቃሉ ተስተማሪነት

የሚቀርበው የቃላት ትምህርት በመማር-ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያጎለብት መሆን አለበት፡፡ የከባድ ቃላት መብዛት በተማሪው ላይ ስነ ልሳናዊና ባህላዊ ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ በአንዳንድ አረፍተነገር ውስጥ ቀደም ብሎ የማያውቃቸው አዳዲስ ቃላት የበረከቱ እንደሆነ፣ የተማሪዎች ትኩረት በሚያነቡት አጠቃላይ ስራ ላይ እንዲያርፍ እንቅፋት ይሆናሉ የመማር ፍላጎትንም ይቀንሳሉ፡፡ የተማሪዎችን ፍላጎት መያዝ የሚቻለው ከተማሪዎች ችሎታ እጅግም ባልበለጠ ቃላት የተጻፈ ስራ የተመረጠ እንደሆነ ነው፡፡

አብዛኞቹ የቋንቋ ማስተማሪያ መጻሕፍት ለየቀረቡበት የክፍል ደረጃ ይመጥናሉ ተብለው የተዘጋጁ ምንባቦችን የያዙ ናቸው፡፡ አዘጋጆች በዚያ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን ዕድሜና የቋንቋ ችልታ አጢነው ምንባቦችን ያሰናዳሉ፡፡ ሆነ ተብሎ ለማስተማሪያነት የሚዘጋጁ ምንባቦች ግን ከሀሳቡ በበለጠ (ቢያንስ በእኩል ደረጃ) ቃል መረጣና አረፍተነገር ግንባታ ላይ ያተኩራሉ፡፡ በድሉ ዋቅጅራ (1996፣12-16) ለማስተማሪያነት የሚቀርበው የቃላት ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን ግላዊ ተሳትፎ የሚያጎለብት እንደመሆኑ መጠን በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተመረጡት ቃላት ያልተሰላቹ ለተማሪዎች ግልጽ፣ ዕድሜያቸውን፣ የትምህርት ደረጃቸውን እና የቀደመ ዕውቀታቸውን መሠረት ያደረጉ በአጠቃላይ ለተስተማሪነት የሚያመቹ መሆናቸውን ከሠነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ ማወቅ ተችሏል፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተመረጡት ምንባቦች ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 10. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱ ምንባቦች

| ምዕራፍ | ርዕስ | የሚገኙበት ገጽ |
|---|---|---|
| አንድ | ቋንቋና የቋንቋ ጥቅም | 1 |
| ሁለት | መከባበር | 16 |
| ሶስት | ኤች አይቪ ኤድስ | 35 |
| አራት | ወጣትነት | 46 |
| አምስት | ሴቶችን ማብቃት | 57 |
| ስድስት | ታዋቂዋ ሴት | 70 |
| ሰባት | ተላላፊ በሽታዎች | 80 |
| ስምንት | የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ | 94 |
| ዘጠኝ | ባህል | 104 |
| አስር | ውሳኔ አሰጣጥ | 113 |

ከሠንጠረዥ 10 መረዳት የሚቻለው በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ለማስተማሪያነት የተቀረጹ ምንባቦች ርዕስ ለተማሪዎች ቅርበት ያላቸው፣ የተማሪዎችን ባህል ከግምት ውስጥ ያስገቡ ናቸው፡፡

### 4.2.1.2.5. ባህላዊ ተላውጦ

አንድ ህዝብ የራሱ ባህል በተመለከተ የተለየ እውቀት እንዲኖረው ይሻል፡፡ እዚህ ላይ ባህል ሲባል የአንድን ህዝብ የተለያዩ የአኗኗር ባህርይ ማለት ነው፡፡ ይህም የህዝቡን ተዋረዳዊ አደረጃጀት (ዕድሩን፣ ደቦውን፣ አስተዳደራዊ ድልድሉን፣ ወዘተ)፣ ተቋማቱን፣ ህጉን፣ ልማደን፣ ሥራውን፣ ስነ-ጥበቡን፣ ሀይማኖቱን፣ ጨዋታውንና የመሳሰሉትን በጠቃላይ እሱነቱን የያዘ ነው፡፡ የአንድ ህዝብ የትምህርት ስርዓትም እያንዳንዱ ግለሰብ ይህን አጠቃላይ ባህልን የሚያውቅበትንና የሚያደንቅበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡ ይህ ለተማሪዎች በራስ የመተማመን ደረጃ

በማሳደግ የባህላቸውን ምንነት ለመገምገምና ለመረዳት ያግዛቸዋል በማለት በድሉ ዋቅጅራ (1996፣8) ያስረዳሉ፡፡

ምሳሌ1. ገጽ 94 እና 104 የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ፣ ባህል) በተከታታይ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ባህል የሚለውን የምዕራፍን ርዕስ ወስደን በምንመለከትበት ጊዜ አመጋብን፣አጊያጊያጥን፣ ባህላዊ ጭፈራ ቁሳቁሶችን፣ የቤት አሰራርን ቀርበው እናገኛላን፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ብሔረሰቦች እንደመኖራቸው መጠን ባህላቸውም በርካታ ነው፡፡ባህል ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ሲሆን ቋንቋን፣ አለባበስን፣ አመጋገብን፣ አኗኗርን… ያካትታል ከዚህ የተነሳ ሁለም ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የባል መገለጫ ሥርዓት አለው፡፡ ተማሪዎቹም የአንድ ብሔረሰብ ባህል ሲቀርብ ከራሳቸው ባህል ጋር እያነጻጸሩ አንድነቱንና ልዩነቱን ማወቅ ይችላሉ፡፡ በህጻናት ጉልበት ብዝበዛ በሚለው ምንባብም የቀረቡት ቃለት ድርጊትን የሚያሳዩ በመሆናቸው ተማሪዎች በአካባቢያው በሚከናወኑ ተገቢ ያልሆኑ ድርጊቶችን የሚያሳዩ በመሆናቸው በቀላሉ የሚረዱዋቸው ናቸው፡፡ በአጠቃላይ እላይ ከቀረቡት ሁለት ምንባቦች ምሳሌ መረዳት እንደሚቻለው በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱት አንዳንድ ቃላት የቀረቡት ወደ ታላሚ ቋንቋ ተተርጉመው ነው፡፡ ስለዚህ የቃላቱ በዚህ ሁኔታ መመረጣቸውና መቅረባቸው ተማሪዎች በራስ የመተማመን ደረጃቸው እንዲያድግ፣ የባህላቸውን ምንነት ለመገምገምና ለመረዳት፣ እንዲሁም በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል፡፡ ስለዚህ የአንድን ባህል ሌላው እንዲያውቅ ከማድረግ አንጻር መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ቃላትን ሲመርጡ የተማሪዎቹን ባህል ከግምት ውስጥ ማስገባት የግድ ይሆናል፡፡ አብዛኞቹ ቃላት የተማሪዎቹን ባህል መሠረት አድርገው የቀረቡ በመሆናቸው ሳይሸማቀቁ በቀረቡት ቃላት መሠረት የታዘዙትን ቃል ነክ መልመጃዎችን መሥራት ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ ተተኳሪ መማሪያ መፅሀፉ አዘጋጆች ቃላቱን ሲመርጡ ባህልን መሠረት አድርገው ስለሆነ ይበል የሚያሰኝ አመራረጥ መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.2.1.3. ከቃላት ትምህርት አደረጃጀት የተመለከቱ መረጃዎች ትንተና

ቃላትን በመምረጥ በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ማካተቱ ብቻ በራሱ ለቃላት ትምህርት በቂ አይሆንም፡፡ የተመረጡ ቃላት በተለያየ መልኩ ካልተደራጁ በቀላሉ ተስተማሪ ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ ለቋንቋ ትምህርትነት የሚውሉ ቃላት በመምረጫ መስፈርት መመረጥ እንዳላቸው በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ የተመረጡት ቃላትም በምን መንገድ መደራጀት እንዳለባቸው አውቆ መልመጃዎችን መቅረጹ አስፈላጊ መሆኑን ማወቅ ይቻላል፡፡ በተተኳሪ መጽሀፍ ውስጥ የተመረጡት ቃላት እንዴት እንደተደራጁ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

#### 4.2.1.3.1. ቃላትን ከቀላል ወደ ከባድ ከማደራጀት አንጻር

McCarthy (1990፣90) የተመረጡ ቃላት ክብደትና ቅለታቸው ታይቶ ከቀላል ወደ ከባድ በተከታታይ መደራጀት እንዳለበት ይገልፃሉ። በተጨማሪም ምሁራን እንደሚያስረዱት ቃላትን ለማደራጀት ስናስብ የተመረጡ ቃላት ከቀላል ወድ ከባድ፣ ከግልፅ ወደ ውስብስብ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ከቀዳማይ ወደ ተከታይ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ፣ ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ መደራጀት እንዳለባቸው በንድፍ ሀሳብ ክለሳ ተመልክቷል። ይህ አይነት አደረጃጀትም ከተማሪዎች የአስተሳሰብ ብስለት ወይም የግንዛቤ ምጥቀት አኳያ እየተስተዋለ ሊከናወን የሚገባ ተግባር ነው። ከመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከተመረጡት ቃላት የትኞቹ ቀድመው ይምጡ? የትኞቹ ቃላት መካከልና የትኞቹ በመጨረሻ ይቅረቡ? ለሚለት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይገባል።

የቃላት ትምህርት ይዘት የታቀደውን ተመርኩዞ ለሚመጣው ደግሞ መሠረት ሆኖ ማለፍ ይኖርበታል። በዚህ መልኩ የተደራጀ የትምህርት ይዘት ተማሪዎች ቀደም ሲል ያካበቱትን ዕውቀት እንዲያጎለብቱና ልምዳቸውን በሥራ ላይ እንዲያውሉ ያግዛቸዋል። የትምህርቱ ይዘት በተማሪዎቹ የቀድሞ ዕውቀት ላይ ተመስርቶ ቀስ በቀስ ስፋትና ጥልቀት እያገኘ የማይሄድ ከሆነ ግን መሰላቸትን ይፈጥራል። ይህ መሰላቸትም በተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ላይ የሚኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ ቀላል አይሆንም።

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡትን የምንባቦችን ርዕስ በምንመለከትበት ጊዜ ለምንባብ ርዕስነት ከተሠጡት ቃላት የየትኛውም የቋንቋ ትምህርት መነሻ ወይም መሠረት ቋንቋ ስለሆነ የቋንቋ ጥቅም የሚለውን ርዕስ በማስቀደም የቃል ክፍሎችን በማስከተል፣ ዐረፍ ነገር የተካተቱ ናቸው። ከዚህ የምንረዳው ቃላት በይዘታቸው ከቀላል ወደ ከባድ መደራጀታቸውን ነው። በተጨማሪም ሠንጠረዥ 10 መመልከት ይቻላል።

በዚህ መልኩ የተደራጀ የትምህርት ይዘት ተማሪዎች ቀደም ሲል ያካበቱትን ዕውቀት እንዲያጎለብቱና ልምዳቸውን በሥራ ላይ እንድያውሉ ስለሚያግዛቸው ተማሪዎች ቃላትን ከተጨባጭ ፍች ጀምረው ወደ ረቂቅ በሂደት የሚማሩትን አደረጃጀት ቢከተሉ የሚቀርቡላቸውን መልመጃዎችን ሳይቸገሩ መስራት ይችላሉ። በመሆኑም መማሪያ መፅሀፉ የቃላት መልመጃዎች ቃላትን ከቀላል ወደ ከባድ ማደራጀት ከሚለው ፅንሰ ሀሳብ አንጻር ብንመረምር ለማደራጀት ተሞክሯል።

## 4.2.1.3.2. ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርጎ ከማደራጀት አንጻር

በክላሳ ድርሳናት እንደተጠቀሰው ቃላትን ለማደራጀት ሌላው መንገድ ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርጎ ማቅረብ ነው፡፡ አንዳንድ ምሁራን እንደሚሉት ቃላት የሚቀርቡበትን መነሻ አድርጎ ማደራጀት የተለመደ ነው፡፡ Grains and Redman (1986፣69) እንደሚገልጹት በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ሥር ሊጠቃለሉ የሚችሉ አንድ ደረጃ የተመረጡ ቃላት የሚያገናኛቸውን ርዕሰ ጉዳይ በመግለጽ እንዲያገለግሉ ከተደረገ በኂላ ቃላቱ በመልመጃ መልክ ተደራጅተው ይቀርባሉ፡፡በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ክፍል አንድ አንብቦ መረዳት አይቀሬ ስለሆነ ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርገው የተደራጁ ቃላትም እንደዚሁ አይቀሬ ሆነው ተደራጅተዋል፡፡ በምሳሌ መልክ ለመጥቀስ ያህል ከመማሪያ መፅሀፍ የሚከተሉትን መልመጃዎች መመልከት ይቻላል፡፡

ምሳሌ1. ምዕራፍ ሶስት፣ ገጽ 41 - 42፣ ምዕራፍ ሶስት ትምህርት አምስት፡- በሚከተሉት ቃላት በመጠቀም አረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

1. ተላላፊ 2. ክትባት 3. ጥንቃቄ 4. ግንዛቤ 5. ማለል 6. ዘገባ 7. ምክር
8. መድሀኒት 9. ምልክት 10. ምርመራ

እላይ የተጠቀሱትን መልመጃዎች ስንመለከት የምንባቡን ርዕሰ ጉዳይ መሠረት አድርገው የወጡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት መልመጃዎች ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርገው የቀረቡ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርገው የቀረቡ መልመጃዎች በርካታ ናቸው፡፡ ስለዚህ መማሪያ መፅሀፉ ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርገው ቃላትን ከማደራጀት አንጻር ጠንካራ ጎን አላቸው፡፡

አጥኚዋ ባደረገችው የሠነድ ፍተሻ እና ቃለ መጠይቅ ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርገው ተደራጅተው የቀረቡ መልመጃዎች በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ መቅረባቸውን አረጋግጣለች፡፡ በአብዛኛው የቀረቡትም ከምንባብ በኂላ በአንብቦ መረዳት ክፍል ውስጥ እንደሆነ ተረጋግጧል፡፡

## 4.2.1.3.3. ፍችን መሠረት አድርጎ ከማደራጀት አንጻር

በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙ የቃላት መልመጃዎች ፍችን መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ለማጣራት አጥኚዋ በምዕራፍ ሁለት ስር ባሰፈራቸው የቃላት አደረጃጀት መስፈርቶች መሠረት ፈትሻለች፡፡ ፍችን መሠረት ማድረግ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ቃላት በአገባባቸው ያላቸውን ግንኙነት የአንድን ቃል ትርጉም በራሱ በቋንቋው ውስጥ ባለው ውስጣዊ

ፍቺ ግንኙነት መሠረት በሌላ መግለጽ ስለሚያስችል ነው፡፡ በዚህ መንገድ ለተማሪዎች መቅረቡ አንድ ቃልን የተለያየ ትርጉም እንዲያውቁ ያደርጋቸዋል፡፡

አጥኚዋ ከሠነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ ባገኘችው መረጃ መሠረት በመፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ የቃላት መልመጃዎች በአብዛኛው ፍችን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ከአጠቃላይ 40 የቃላት መልመጃዎች ውስጥ 18 የቃላት መልመጃዎች ፍችን መሠረት ያደረጉ ሲሆን ይህም የሚያመለክተው 45% ያህልን ሽፍነው ይገኛሉ፡፡ የቀረቡበት ስልትም በአብዛኛው ተማሪዎች በአውድ ትርጉሙን እንዲረዱ፣ በተመሳሳይና በተቃራኒ ፍች እንዲሁም እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችን መሠረት በማድረግ የተደራጁ ናቸው፡፡ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የእማሬያዊና ፍካሬያዊ መልመጃዎች የቃላት መልመጃውን 6% ይዘው የተደራጁ በመሆናቸው በመማሪያ መፅሀፉ ፍችን መሠረት ያደረገ የቃላት አደረጃጀት መኖሩን ያሳያል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎችን በይበልጥ ለማሳተፍ በቂ አይደሉም፡፡ ፍችን መሠረት አድርጎ ቃላት ማደራጀትን በተመለከተ የሚከተሉትን ምሳሌዎች ለአብነት በመውሰድ እንመልከት፡፡

**ሠንጠረዥ11. የቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መልመጃዎች**

| ምዕራፍ | ይዘት | ገጽ |
|---|---|---|
| ምዕራፍ ሰባት | የሚከተለትን ቃላት እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ጻፉ | 89 |
| ትምህርት አምስት | የተሠጡትን እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች በአረፍ ተነገር ውስጥ አስገብቶ ማሳየት | 89 |

ከሠንጠረዥ 11 መረዳት እንደሚቻለው በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ቃላት በእማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍችም እንደተደራጁ ነው፡፡ ነገር ግን በምዕራፍ ሰባት ስር ብቻ 2 የእማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች መልመጃዎች መኖራቸው ተማሪዎች አንድ ዓይነት ይዘት በተደጋጋሚ ሲማሩ ሊሰለቹ ስለሚችሉ በየምዕራፉ ተበታትኖ ቢቀርቡ መልካም ነው፡፡ ቃላት በእማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍች ብቻ ሳይሆን በተመሳስሎና ተቃርኖ ፍችም ተደራጅተው ቀርቧል፡፡

ምሳሌ1. ምዕራፍ ሰባት፣ ገጽ 88፣ ክፍል አምስት፣ ትምህርት አምስት ቃላት በአንድ ፍች ብቻ ላይወሰኑ ይችላሉ፡፡ አንዳድ ቃላት እንደ አገባባቸው ፍችያው ሊለያይ ይችላል፡ አስር እማሬያዊና ፍካሬያዊ ፍቺ ያሏቸው ቃላት ፈልጉና ፍቻቸውን በመተንተን ተለማመዱ፡፡

የሚከተሉት ቃላት ከተረቱ የወጡ ናቸው፤ የእያንዳዳቸውን ፍቺ ተናገሩ፡፡

1. የባስ 2. ፎከረ 3. ሲጋጭ 4. ተጸጸተ 5. ፍርሀት 6. እረኝነት 7. አስተጋባ

እላይ ካለው መልመጃ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች በተሰጣቸው ምሳሌ መሠረት የቃላቱን ተመሳሳይ በፍቺ ከማደራጀት አኳያ እንዲሰሩ ለማድረግ ታስቦ የቀረበ ነው፡፡

ምሳሌ 2. ምዕራፍ ሶስት፣ ገጽ 40፣ መልመጃ ሶስት

በ "ሀ" ክፍል ለተዘረዘሩት ቃላት በ "ለ" ስር ከተሰጡት ቃላት ተቃራኒ ፈልጉላቸው ፡፡

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. በሽተኛ | ሀ. ግድ የለሽ |
| 2. ከሳ | ለ. ከተማ |
| 3. ድካም | ሐ. ተጎጂ |
| 4. ጠንቃቃ | መ. ማሳጠሪያ |
| 5. ማራዘሚያ | ሠ. አስደሳች |
| 6. ቀነሰ | ሰ. ጨመረ |
| 7. ለገሰ | ሽ. ጤነኛ |
| 8. አስከፊ | ቀ. ብርታት |
| 9. ተጠቃሚ | በ. ወፈረ |
| 10.ገጠር | ተ.ትውልድ |

ከላይ የቀረቡትን መልመጃዎች እንደ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ነው እንጂ በአብዛኛው በመማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት ቃላት ፍችን መሠረት በማድረግ የቀረቡ መሆናቸውን ከሠነድ ፍተሻና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.2.1.3.4. ቅርፅን መሠረት አድርጎ ከማደራጀት አንጻር

የቃላት አደረጃጀት ስልት በክለሳ ድርሳናት እንደተገለጸው ቅርፅን መሠረት አድርጎ ማደራጀት ነው፡፡ ሌላው McCarthy (1990፣ 99) እንደሚያስረዱት በቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ

የሚካተቱ ቃላት አመሰራረት እንደሚያሳየው ቃላትን በየጊዜው በተወሰነ መጠን እየመሠረትን በሄድን ቁጥር በቋንቋ ውስጥ ተማሪዎች ብዙ አዳዲስ ቃላት እንዲፈጥሩ ያስችላቸዋል፡፡ ቃላትን በቅርጽ ማደራጀት ምስረታና ድርብ ቃላትን እንደ አንድ አሀድ ለመማርና የቃላቱን ምዕላደዊ አወቃቀር እየበታተኑ ለመመርመር እንዲሁም ፍቺን ከተዋቃሪ ቅርጾች ጋር ለማዛመድ የሚያስችል ቅርጻዊ አደረጃጀት መከተል፣ ለትምህርት የሚቀርቡትን ቃላት ለመረዳትና ለማፍለቅ አስተዋጽኦው የጎላ መሆኑን የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

ነገር ግን በተተኳሪ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ድርብ ቃላትን የሚመለከት መልመጃ አለመካተቱ እንዲሁም ፍችን ከተዋቃሪ ቅርጾች ጋር ማዛመድን የሚመለከት መልመጃ በመማሪያ መጽሀፉ አለመቅረቡ የመማሪያ መፅሀፉ ደካማ ጎን ነው፡፡ ምስርታ ቃላትን በተመለከተ እንደ አንድ አሀድ ለመማርና የቃላቱን ምዕላዳዊ አወቃቀር እየበታተኑ ለመመርመርም የቀረቡ መልመጃዎች ውስን ናቸው፡፡

ምሳሌ1. ገጽ 87 በሚከተሉት ሠንጠረዥ የቀረቡትን ምሳሌዎች መሰረት በማድረግ፣ በቀረቡት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ቅጥያዎች በመለየት የእርባታ ወይም የምስረታ ቅጥያዎች መሆናቸውን በምሳሌው እንደተመለከተው የ ‘x’ ምልክት አድርጉ፡፡

**ሠንጠረዥ12. የእርባታ ወይም የምስረታ ቅጥያዎች**

| ተ.ቁ | ግስ | የእርባታ | የምስረታ |
|---|---|---|---|
| 1 | ፈለግህ | | |
| 2 | ፈለገች | | |
| 3 | ይፈልጉ | | |
| 4 | ፈላጊ | | |
| 5 | ፍለጋ | | |
| 6 | ፍላጎት | | |

እላይ ከተሰጠው መልመጃ መረዳት እንደሚቻለው አንድን ግስ በመበታተን የተለያዩ ተግባራት ያላቸውን ግሶች በቅርጻቸው ማደራጀትን የሚመለከት ነው፡፡ በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ በዚህ

አኳሃን የተደራጁ መልመጃዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ መሆን ተማሪዎች የቃላትን ቅርጻዊ አደረጃጀት አውቀው መልመጃዎችን እንዳይሰሩ ሊያደርጋቸው ይችላሉ፡፡ በአጠቃላይ በተተኳሪ መማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የምስረታ መልመጃዎች ብዛት አነስተኛ ስለሆነ ቅርጽን መሠረት አድርጎ ቃላትን ከማደራጀት አንጻር መማሪያ መፅሀፉ ድክመት እንዳለው ከሠነድ ፍተሻ እና ከቃለ መጠይቅ ማወቅ ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በትግራይ ክልል በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ መገምገም ነው። ይህንን አጠቃላይ አላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሶስት ንዑስ አላማዎች አሉት:: እነሱም፡-

- የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለመምረጥ በስራ ላይ የዋሉት የቃላት ይዘት መምረጫ መስፈርቶች ተገቢ መሆን አለመሆናቸውን መገምገም፤
- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተዘረዘሩት የቃላት ትምህርቶች ተገቢ ማቅረቢያ ስልቶችን በመጠቀም መቅረብ አለመቅረባቸውን መፈተሽ፤
- በተተኳሪው መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት መገምገም የሚሉት ናቸው።

እነዚህን ንዑስ አላማዎች እና የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ለማሳካት በ2015 ዓ.ም በትግራይ ክልል ስራ ላይ የዋለው የ8ኛ ክፍል አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ በሰነድ ፍተሻ በመገምገም እንዲሁም የመጽሀፉን መምህራን ቃለመጠይቅ በማድረግ የተገኙት መረጃዎች ተሰብስበው ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል። የትንተናውን ውጤት መሰረት በማድረግም የሚከተለው ማጠቃለያ ላይ ተደርሷል። ከጥናቱ ንዑስ አላማዎች የመጀመሪያው የጥናቱ አላማ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ለመምረጥ በስራ ላይ የዋሉት የቃላት ይዘት መምረጫ መስፈርቶች የተማሪውን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ ፣ የቃላት የድግግሞሽ መጠን፣የቃላት የፍች ሽፋን፣የቃሉ ተስተማሪነት እና ባህላዊ ተላውጠ ያካትታል።

ሁለተኛው የጥናቱ ንዑስ  አላማ በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብ መገምገም የሚል ሲሆን ይህንን ዓላማ ለማሳካት ጥናቱ በምሁራን የተገለጹ የቃላት ትምህርት ይዘት ማቅረቢያ መስፈርቶችን ቃላትን በአውድ ማቅረብ፣ በፍች ዝምድና ማቅረብ፣ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ማቅረብ፣ ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ማቅረብና ከክሂል ትምህርቶች ጋር ማቅረብ የሚሉት ይገኛሉ።

የመጨረሻው የጥናቱ ዓላማ በመማሪያ መጽሀፉ የተካተቱት የቃላት ትምህርት ይዘቶችን አደረጃጀት መገምገም የሚለው ነው። ይህንን አላማ ለማሳካት ጥናቱ በምሁራን የተገለጹ የቃላት

ትምህርት ይዘት ማደራጃ መስፈርቶችን ጥቅም ላይ አውሏል። እነዚህ መስፈርቶችም ቃላትን ከቀላል ወደ ከባድ ማደራጀት ፣ርዕሰ ጉዳይን መሠረት አድርጎ ማደራጀት፣ፍችን መሠረት አድርጎ ማደራጀት እና ቅርፅን መሠረት አድርጎ ማደራጀት የሚሉ ናቸው። በመሆኑም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች የቃላት ትምህርት ይዘት አደረጃጀት መስፈርቶች መሰረት አድርገን ስንመለከት ቃላትን በአውድ ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች አውዳዊ አቀራረብን መሰረት አድርገው በጥሩ ሁኔታ የተዘጋጁ መሆኑን፤ በፍች ዝምድና ከማቅረብ አንጻር በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ተግባራት አቀራረብ ችግር ያለበት መሆኑን፤ በመዝገበ ቃላት አስደግፎ ከማቅረብ አኳያ በመማሪያ መጽሀፉ በመዝገበ ቃል በመደገፍ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በቁጥር አነስተኛ ከመሆናቸውም በላይ በግልጽ መመሪያ አለመቅረባቸው ትልቅ ክፍተት መሆኑን፤ ግልፅ በሆኑ መመሪያዎች ከማቅረብ አኳያ መጽሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት ተግባራትን በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች የማቅረብ ክፍተት ያለበት መሆኑን፤ ከክሂል ትምህርቶች ጋር አቀናጅቶ ከማቅረብ አንጻር መጽሀፉ ለክሂሎች ቅንጅታዊ አቀራረብ የተሻለ ትኩረት የሰጠ መሆኑን፤ በአጠቃላይ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በአብዛኛው በምሁራን የተገለጹትን የቃላት ትምህርት አቀራረብ መስፈርቶችን መሰረት በማድረግ የቀረቡ መሆናቸውን የመረጃ ትንተናው ውጤት ያመለክታል።

## 5.2. አስተያየት

ከዚህ በላይ በማጠቃለያው የተገለጹትን የጥናቱን ውጤቶች መሰረት በማድረግ መቀጠል የሚገባቸው የመጽሀፉ ጠንካራ ጎኖች መኖራቸው ሳይዘነጋ ችግር በታየባቸው የመጽሀፉ የቃላት ይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ አጥኚዋ ከዚህ በታች ያሉትን አስተያየቶች ሰንዝራለች።

- የቃላት መረጣው ሲካሄድ በተቻለ መጠን ቋንቋን ለማስተማር ለሚነደፍ መርሀ ግብር እንዲውሉ በመስኩ ምሁራን ለተሰነዘሩት የቃላት ይዘት መምረጫ መስፈርቶች ሁሉ ትኩረት ቢሰጥ፤
- የቃላት ትምህርት አደረጃጀትን በተመለከተም ምንም እንኳ በመጽሀፉ ውስጥ ከሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አንጻር፣ በአንድ ምንባብ ውስጥ በመገኘታቸውና ስለ ቃላት የተወሰነ ግንዛቤ

ያስጨብጣሉ በመባላቸው የተደራጁ ቢሆንም ግን ምሁራን እንደሚሉት የፍች ገጽታቸውን፣ የቅርጻቸውን መመሳሰል ወዘተ ከግምት ያስገባ አደረጃጀትም በሰፊው ተግባራዊ ቢደረግ፣

- በመፅሀፉ የቀረቡ የቃላት ትምህርት ይዘቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ጋር ተጣምረው ቢቀርቡና በመዝገበ ቃላት አጠቃቀም ጥበብ ላይ ያተኮሩ መልመጃዎች በጥራት ተቀርፀው ቢካተቱ፤የሚሉት አስተያየቶች ጥናቱ ሲጠናቀቅ በተተኳሪ መማሪያ መፅሀፉ የቃላት ትምህርት ይዘት መልመጃዎች ላይ ከታዩ ድክመቶች በመነሳት በአጥኚዋ የቀረቡ ናቸው፡፡

# ዋቢዎች


ማገረው አለሙ (2003)*" ዘመናዊ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማርያ ዘዴ".አዲስ አበባ፡አልፋ ማተሚያ ቤት።*

ምንውየለት ደነቀው (2005) *"በአማራ ክልል በስራ ላይ ያሉት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የቃላት ትምህርት የይዘት አመራረጥ፣ አደረጃጀና አቀራረብ ግምገማ"። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ (ያልታተመ)።*

ሞላ አጽብሃ (2003) *"በትግራይ ክልል ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቃላት አመራረጥ፣ አደረጃጀትና አቀራረብ ትንተና" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሁለተኛ ዲግሪ መሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።*

ሲሳይ መላኩ(1990) *"በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ቃላትን የማስተማር ብቃትን መገምገም" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)።*

በድሉ ዋቅጅራ (1996)። *በስነ-ጽሁፍ ቋንቋን ማስተማር። ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።*

በኢትዮጵያን የዩኒቨርሲቲ መምህራን የውይይት ማህበር የተዘጋጀ። (1980)። *ተራማጅ መዝገበ ቃላት። አዲስ አበባ፣ ሴንተራል ማተሚያ ቤት።*

ባየ ይማም (1987) *"የአማርኛ ሰዋስው"። አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ዴ።*

________ 2000። *የአማርኛ ሰዋስው (የተሻሻለ ሁለተኛ እትም)። አዲስ አበባ፣ ኢሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.ማህበር።*

ብርሀኑ ገበየሁ። (1999)። *የአማርኛ ሥነግጥም። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።*

አለማዝ ዮሐንስ (2012). *"የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ የቃላት አደረጃጀትና አቀራረብ ፍተሻ" በሚል ርዕስ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረበውን ጥናት (ያልታተመ)*

አበባው አረጋ (2021). *"በኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ሚና." ማህበራዊ ሳይንስ ጆርናል, 27(1), 78-92.*

አብይ ይመር። 1991። *የአማራው ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት የቃላት ትምህርት ይዞታ ግምገማ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ! ለኢትዮጲያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል ለአርት ባችለርዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት።(ያልታተመ)*

እንግዳው ሙሉዓለም (1993). *ቀዳሚው ትውልድ የአማርኛ ሰዋሰው። አዲስ አበባ፣ ሜጋ።*

ዘሪሁን አስፋው (1996). *የስነ-ጽሑፍ መሠረታውያን። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።*

ያለው እንዳወቀ፡፡ 1998ዓ.ም፡፡ *የምርምር መሰረታዊ መርሆች አተገባበር፡፡ ባህርዳር! ባህርዳር ዩነቨርሲቲ፡፡*

________2004፡፡*የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር (ሦስተኛ እትም)፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡*

ዳኒኤል ተኹሉ፡፡1997::*መፅናዕቲ ክፍሊ ቃላት፡፡ ትግራይ፣ መቐለ ፣ቤት ሕትመት ሜጋ መቐለ፡፡*

ጌታሁን አማረ፡፡ 1990፡፡ *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡*

Atkins, J and etal. (1996). *Skill Development methodology, (part II). Addis Ababa. Addis Ababa Publisher.*

Allen, V.F. (1983). *Techniques in teaching vocabulary. Oxford; Oxford University Press.*

Aweke Ayalneh. (2016). *Assessing The Practice Of Teaching Vocabulary: The Case Of Haramaya University Model School Grade Nine Students in Focus, MA Thesis. Haramaya University (Unpublished).*

Bauer, L. (1998). *Vocabulary. London and New York; Routledge.*

Carter, R. and McCarthy, M. 1988. *Vocabulary and language teaching. NewYork: longman.*

Cohen, L. and Lawrence, M. 1994. *Research methods in Education. London/*

*New York; Routhledge.*

Dubin, F. and Olshtain, E. (1986). *Course design; Developing programs and materials for language learning, Cambridge: Cambridge University Press.*

Elley, W. (1989). *Tailoring the evolution to fit the context. In Johnson, R. (Ed.), The second language curriculum (Vol. 21, No. 2, pp. 53-60). Cambridge: Cambridge University Press.*

Gairns, R. and S. Redman. (1986). *Working with Words; Aguide to Teaching and Learning Vocabulary. Cambridge: CUP.*

Harmer, J. (1994). *The practice of English language teaching. London. New York. Longman. Group (UK) Ltd.*

Hutchinson, T.,Torres, E. (1994). *The textbook as agent of change ELT Journal, 48(4), 315-328.*

Krippendorf, K. (2004). *Content Analysis: An introduction to Its Methodology (2nd ed.). Sage Publications, Inc.*

Koul, L. 1993. *Methodology of Educational Research. 2nd Rev. ed. New Delhi Vicas publishing house put. Ltd.*

Lewis, M. and Hill, J. 1985. *Practical Technique for language teaching London: Commercial Colours Press.*

Lewis, M. (1993). *The Lexical Approach. London: Comercial Colour Press.*

Lawson, M., & Hogben, D. (1996). *The Vocabulary-Learning Strategies of Foreign-Language Students. Language Learning, 46, 101-135.*

McCarten, J. (2007). *Teaching Vocabulary. Cambridge: Cambridge University*

*Press.*

McCarthy, M. (1990). *Vocabulary. Oxford. Oxford University Press*.

Morgan, J. and Rinvolucri, M. (1986). *Vocabulary; Oxford: CUP.*

Nation, I. S. P. (2001). *Learning vocabulary in another language. Cambridge: Cambridge University Press.*

Nation, P. and Cody, J. 1988. *Vocabulary and reading In Carter, R. and McCarthy, M. (eds). Vocabulary and Language Teachung. New York: Longman Group (UK)* Limited.

Nunan, D. (1991). *Language teaching Methodology: A text book for language teachers. Edinberugh: Pearson Education Ltd.*

Rebert, A. 1985. *Dictionary of Psychology. London; Penguin Books.*

Richards, J. C. (2001). *The context of language teaching. New York: Cambridge University Press.*

Richards, J. C., Rodgers, T. S. (1995). *Approaches and methods in language teaching. Cambridge University Press.*

______(2014). *Approaches and methods in language teaching (3rd ed.). Boston, MA: Cengage Learning.*

River, W. 1994. *Communicating naturally in second language (8th ed.). Cambridge: Cambridge University Press.*

*Seal,B.D (1991). Vocabulary Learning and Teaching. In M. Celce-Murcia (Ed.), Teaching English as a Second or foreign Language (pp.296-311). Boston, MA: Heinle & Heinle Publication.*

Sheldon, L.E. (1988). *Evaluating ELT textbooks and materials. English Language Teaching Journal, 42(4), 237-246.*

Ur, P. (1996). *A Course in language teaching, practice and theory. Cambridge: CUP.*

_______2009. *A course in language teaching practice and theory. Cambridge: Cambridge University Press.*

Wallace, M. (1988). *Teaching Vocabulary. Chicago: University of Chicago Press.*

*Wilkins, D.A. (1972). Linguistics in language teaching. London: The English Language Book Society and Edward Arnold (Publishers) Ltd.*

www.ccsenet.org/elt. *Effectiveness of Structural Method of Teaching Vocabulary. Vol.3, No.3; September 2010. Published by Canadian Center of Science and Education.*

# አባሪዎች

## ቃለ መጠይቅ

በመቐለ ዩነቨርሲቲ

የህብረተሰብ ሳይንስና ቋንቋዎች ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የክረምት ድህረ ምረቃ መርሃ-ግብር

በ2015 ዓ.ም በትግራይ ክልል ስራ ላይ በዋለው የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ ለሚጠቀሙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የቀረበ ቃለ-መጠይቅ

ውድ መምህራን፡- ይህ ቃለ መጠይቅ የተዘጋጀው በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን ለፈቱ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሐፍ የቃላት ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ለመገምገም በሚል ርዕስ ለሚደረገው የሁለተኛ ድግሪ ከፊል ማሟያነት ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ነው፡፡ ለዚህም እርስዎ የሚሰጡኝ መረጃ በጣም ያስፈልገኛል፤ በውይይታችን የምንለዋወጣቸው ሀሳቦች ምስጢራዊነት የተጠበቀና ለዚህ ጥናት ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

### አባሪ አንድ

**ክፍል አንድ**፡- ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው መምህራን መረጃ

ውድ ጊዜዎን ሰውተው ለሚያደርጉልኝ ትብብር ከወዱሁ አመሰግናለሁ!

1. ቃለ መጠይቁ የተጀመረበት ቀን________ሰዓት_________ቦታ_________ያበቃበት ሰዓት___________
2. ፆታ__________
3. ዕድሜ__________
4. የትምህርት ደረጃ__________
5. የሰለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ አብይ________________________ንኡስ ______________________
6. የአገልግሎት ዘመን __________________

**ክፍል ሁለት**፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃለ-መጠይቆች ትክክል ነው የሚሉትን ሀሳብ እንዱሰጡን በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

1. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች መልመጃዎች አውድን እና በግልጽ መመሪያዎችና ምሳሌዎች  መሠረት አድርገው የቀረቡ ናቸው ብለው ያስባሉ? ሀሳብዎን አብራርተው ይግለፁ፡፡
2. በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡት ቃላት ባላቸው የፍች ዝምድና አማካይነት ቀርበዋል? ማለትም (በተመሳስሎና ተቃርኖ፤ በቃላት የማጠቃለልና የመዘርዘር ሁኔታ፤ ከቃላት አብሮ ተሰላፊነት አንጻር)
3. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት የቃላት ትምህርት ይዘቶች በመዝገበ ቃላት ተደግፈው ቀርበዋል ብለው ያስባሉ?
4. በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የቀረቡት ቃላት ይዘት መልመጃዎች ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል?
5. የቃላት ትምህርት ይዘት አመራረጥ የተማሪውን ፍላጎትና የትምህርት ደረጃ፣ የቃላት የፍች ሽፋን፣ የቃሉ በቅርብ መገኘት፣ የቃሉ ተስተማሪነት፣ የቃሉ ባህላዊ ተለውጦን ወይስ የቃላት የድግግሞሽ መጠንን መሠረት ያደረገ ነው?
6. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቃላት ትምህርት ይዘቶች የተደራጁት ከቀላል ወደ ከባድ፣ በሚያወሱት ርዕሰ ጉዳይ፣ በፍቺዎቻቸው ወይስ በቃላት ቅርፅ አማካይነት ነው?

**ማረጋገጫ**

እኔ ከዚህ በታች ስሜንና ፊርማዬን ያስቀመጥኩት በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር የድህረ-ምረቃ ተማሪ ሲሆን ይህ ጥናት የራሴ ስራ መሆኑንና በስራው ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ምንጮች በሙሉ በዋቢ መፃህፍት ላይ የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- ኣብሪሃ ኣሰፋው ኣድሀና

ፊርማ ------------------------------------------

የማስረከቢያ ቀን ------------------------------